***የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ!***

***የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!***

***የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!***

***ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!***

***ክቡራትና ክቡራን!***

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና 267/2011 አንቀጽ 6 (2) (ሐ) እና አንቀጽ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልጽ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የሚደነግግ በመሆኑና ይህን ሪፖርት ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እየገለፅኩ መ/ቤታችን በ2010/2011 በጀት ዓመት ያከናወናቸውን የክዋኔ ኦዲት ስራዎች የተጠቃለለ ሪፖርት ለተከበረው ጉባዔተኛ በንባብ አቀርባለሁ፡፡
2. በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን በ2010/2011 በጀት ዘመን ኦዲት አድርጎ ያጠናቀቃቸው የ20 መ/ቤቶች የመደበኛ እና የክትትል ኦዲት ቢሆንም ከጊዜ አንጻር ለዚህ ም/ቤት በንባብ የሚቀርበው ግን የ10 መ/ቤቶች የመደበኛ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ብቻ ነው፡፡
3. የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ስራዎች በተመደበላቸው ሃብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናዎን ኦዲት ነው፤
4. በዘገባ ሪፖርቱ ከተዘጋጁት የክዋኔ ኦዲቶች መካከል በአብክመ ከተማ ል/ቤ/ኮ ቢሮ የሊዝ ሂሣብ አስተዳደር፤በክልሉ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የስራ እድል ፈጠራ ዉጤታማነት፣ የኮሌጆች ግንባታና ግብዓት አቅርቦት እና የሼድ ግንባታ፤የክልሉ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እና የክልሉ ቤቶች ልማት ድርጅት የቤቶች አስተዳደርና ህንፃ ግንባታን፤የአብክመ ትምህርት ቢሮ የኮሌጆች ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም፣የስልጠና ሂደት እና የሰልጣኞች ውጤታማነት የስራ እንቅስቃሴ፤ በክልሉ የጤና ጥበቃ ቢሮ የእናቶች እና ህፃናት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፤ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ «የቅርስ ጥበቃ፣የቱሪዝም ልማትና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አፈጻጸም»፣ የክልሉ ግብርና ቢሮ የሰብል ልማት፤ጥበቃና ቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በሚመለከት ያለው አፈፃፀም፤ የአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር ስራዎች ዉጤታማነትን፤ በአብክመ ከተማ ል/ቤ/ኮ/ቢሮ የከተሞች ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ግንባታ ፕሮግራም አፈፃፀምና አስተዳደር የተመለከቱ ሲሆን የእያንዳንዱን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት የክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ውጤት የያዘ አስቀድሞ ለየመ/ቤቶቹና ለተቆጣጣሪ አካላት የማሻሻያ አስተያየት ያካተተ የ20ዎቹም የኦዲት ሪፖርት እንዲደርሳቸው አድርገናል፡፡ የመደበኛ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርቱ ከተላከላቸው 10 መ/ቤቶች ውስጥ 6ቱ በወቅቱ ምላሽ የሰጡ ሲሆን

ቀሪዎቹ 4ቱ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት 30/5/2012 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡ በዚህ አጭር ሪፖርት ከግኝቶች ጉልህነትና ከጊዜ አንጻር ስፋቱን ለመመጠን ሲባል ለተከበረው ም/ቤት ለንባብ የቀረበው በመደበኛው ኦዲት የተገኙ የተመረጡ ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ብቻ በመሆኑ ዝርዝሩን ለማየት ሙሉ ሪፖርቱን ማንበብ ይጠይቃል፡፡

5. ለክዋኔ ኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዘርፎቹ እንዲመሩባቸው መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በህግ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት፣የየመ/ቤቶች የስራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ከየመ/ቤቶቹ ደንበኞች/ ተገልጋይች ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ስራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የኦዲት ስራውም ዓለም አቀፍ እና አገራዊ የክዋኔ ኦዲት አሰራር መርሆችና ስታንዳርዶችን ተከትሎ የተከናወነና ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ግኝቶች በናሙና በተመረጡ ዞኖችና ከተሞች እንዲሁም ወረዳዎች ብቻ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ እያሳሰብኩ ከዚህ በመነሳት ዋና ዋና ግኝቶችን በአጭሩ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

## I. በአብክመ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ የሊዝ ሂሣብ አስተዳደርን በተመለከተ፤

**6. በጨረታ አግባብ የተላለፉ የሊዝ ቦታዎች ጨረታ ባሸነፉበት ዋጋ መሰረት ዉል መያዙን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ግኝቶች ተስተውለዋል፡፡**

**ሀ. ደብረ ማረቆስ ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮን/ አገልግሎት ጽ/ቤት**

6.1 በ2010 በጀት ዓመት በ1ኛ ዙር የማህበራዊ የሊዝ ጨረታ ቦታ ለእልፍኝ የገበያ ማዕከል ሲሰጥ በ1 የቦታ ኮድ፤1520.25 ካ.ሜ የቦታ ስፍት፣አሸናፊው ለካ.ሜ የሞላው ዋጋ ብር 6,135.00፣ጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ ብር 9,326,733.75 ሆኖ ሳለ ከጽ/ቤቱ ጋር የውል ስምምነት ሰነድ ላይ በብር 7,326,733.75 ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **2,000,000.00** ዉል ሳይያዝ የተገኘ መሆኑ፣

6.2 በ2010 በጀት ዓመት በ1ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለአሸናፊው ሲሰጥ በ1 የቦታ ኮድ፤ 150 ካ.ሜ የቦታ ስፍት፣ ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር 5621፣ ጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ ብር 843,150 ሆኖ ሳለ ጨረታውን አሸንፈው ከጽ/ቤቱ ጋር ውል የተያዘው ከአሸነፈበት ዋጋ ተቀንሶ ለካ.ሜ በብር 5361 ሲሆን የፈጸመው ቅድሚያ ክፍያ ብር 84,350 ተቀንሶ ውል ሰነዱ ላይ ቀሪ ክፍያ ብር 758,800 መያዝ ሲገባው ብር 719,800 ተብሎ ውል ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **39,000.00** ዉል ሳይያዝ መገኘቱ፤

6.3 2009 በጀት ዓመት በ2ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ለሴንተራል የገበያ ማዕከል ቦታ ሲሰጥ ለ3 የቦታ ኮዶች፤ ለ491 ካ.ሜ የቦታ ስፍት፣ ጨረታውን አሸንፈው ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር

6555.48 ሆኖ ሳለ ከጽ/ቤቱ ጋር ውል የተያዘው ከአሸነፈበት ዋጋ ተቀንሶ ለካ.ሜ በብር 6537.66 ሲሆን የከፈለው የቅድሚያ ክፍያው ብር 321,875 ተቀንሶ ቀሪ ክፍያ ብር 2,896,865.68 ውሉ መያዝ ሲገባው ብር 2,888,116.06 ተብሎ ውል ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **8,749.62** ውል ሳይያዝ የተገኘ መሆኑ፣

6.4 በ2009 በጀት ዓመት በ2ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለአሸናፊው ሲሰጥ ለ1 የቦታ ኮድ 150 ካ.ሜ የቦታ ስፍት፣ አሸንፈው ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር 4,350፣ ጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ ብር 652,500 ሆኖ ሳለ ውል ሲይዙ ብር 65,250 ቅድሚያ ክፍያ ተቀንሶ ውል ሰነዱ ላይ ቀሪ ክፍያ ብር 587,250 መሆን ሲገባው ብር 582,250 ተብሎ ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **5,000** ውል ሳይያዝ የተገኘ መሆኑ፣

6.5 በ2009 በጀት ዓመት በ2ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለሴንተራል የገበያ ማዕከል ቦታ ሲሰጥ ለ3 የቦታ ኮዶች፤ 457.42 ካ.ሜ የቦታ ስፍት ፣አሸናፊ ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር 6,541.127 ሆኖ ሳለ ከአሸነፈበት ዋጋ ተቀንሶ ለካ.ሜ በብር 6537.66 ተብሎ ውል ስለተያዘ በጠቅላላ ዋጋ ልዩነት በማነስ ብር **1585.87** ውል ስለተያዘ፤

**በከተማው በጠቅላላ** ከውሉ በማነስ ብር **2,054,335.49** ውል ሳይያዝበት ተገኝቷል።

**ለ. ደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮን/አገልግሎት ጽ/ቤት**

6.6 በ2007 በጀት ዓመት በ1ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለአሸናፊው ሲሰጥ የ1 የቦታ ኮድ 112.75 ካ.ሜ የቦታ ስፍት ፣ ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር 4,000 ጠቅላላ ዋጋ ብር 451,000 ሲሆን ብር 67,650 ቅድሚያ ክፍያ ተቀንሶ ውል ሰነዱ ላይ ቀሪ ክፍያ ብር 383,350 መሆን ሲገባው ብር 89,750 ተብሎ ውል ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **293,600** ውል ሳይያዝ የተገኘ መሆኑ፣

6.7 በ2008 በጀት ዓመት በ2ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለአሸናፊው ሲሰጥ ለ1 የቦታ መለያ ቁጥር ደረጃ 2፤ 200 ካ.ሜ የቦታ ስፍት፣ አሸንፈው ለካ.ሜ የሞላው ዋጋ ብር 3385.21፣ ጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ ብር 677,042 ሆኖ ሳለ ውል ሲይዙ ብር 67,704.20 ቅድሚያ ክፍያ ተቀንሶ ውል ሰነዱ ላይ ቀሪ ክፍያ ብር 609,337.80 መሆን ሲገባው ብር 600,337.80 ተብሎ ውል ስለተያዘ ልዩነት በማነስ ብር **9,000.00** ውል ሳይያዝ የተገኘና ሌላ በዚሁ ተመሳሳይ የታየ ልዩነት ብር 1875.00 ጨምሮ፣ በከተማው በድምሩ ከውል በታች በማነስ ብር **302,600** ተይዞ ተገኝቷል።

**ሐ. ጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ**

6.8 በ2010 በጀት ዓመት አንድ የከተማ ነዋሪ ለመኖሪያ አገልግሎት በጨረታ ቦታ ሲያገኙ የቦታ ስፋት 150 ካ.ሜ፣ አሸንፈው ለካሬ ሜትር የተሞላው ዋጋ ብር 7555 የቦታው ጠቅላላ ዋጋ ብር 1,133,250 ሲሆን ቅድሚያ ክፍያ ብር 124,657.50 ተቀንሶ ቀሪ ክፍያ ብር 1,008,592.50 ሆኖ

ዓመታዊ ክፍያ ብር 25,214.81 በየዓመቱ እስከ 40 ዓመት እየተከፈለ እንደሚጠናቀቅ ዉል መያዝ ሲገባው ብር 20,171.85 የሚከፈል ተብሎ ዉል ስለተያዘ ልዩነት 5,042.96 ከዓመታዊው ክፍያ የሚቀር ሲሆን ለ40 ዓመት ብር **201,718.40** ከውሉ ሰነዱ ላይ ዓመታዊ ክፍያው ተቀንሶ ውል በመያዙ ሳይከፈል እንዲቀር የተመቻቸ ሁኔታ መኖሩ፣

6.9 በ2005 በጀት ዓመት ለንግድ አገልግሎት የሚውል 641 ካ.ሜ ቦታን ለአንድ የግል ሪል ስቴት ማህበር ለካ.ሜ በብር 2,500 ሂሳብ ጠቅላላ ዋጋ ብር 1,602,500 ውል ተይዞ መተላለፍ ሲገባው ውሉ ላይ የተቀመጠው የቦታ ስፋትና ለካ.ሜ የቀረበው ዋጋ ምንም ዓይነት ለውጥ በሌለበት ሁኔታ ጥቅል ዋጋውን ብር 1,328,500 በማድረግ ቅድመ ክፍያውን ብር 132,850 እንዲሁም ብር 47,826 በየዓመቱ እንዲከፍል በሚል ውል በመያዙ የ109.6 ካ.ሜ ቦታ ዋጋ ብር **274,000.00** ውል ሳይያዝ ከ5 ዓመታት በላይ ቆይቶ የተገኘ መሆኑ፣

6.10 በ2006 በጀት ዓመት ለመኖሪያ አገልግሎት የሚውል ለ1 የመለያ ኮድ ቁጥሩ፤ 200 ካ.ሜ ቦታ በጥቅሉ በብር 322,200 **ተጫራቹ** አሸነፎ ቀሪ ክፍያውን በ25 ዓመት ውስጥ አጠቃሎ ለመክፈል ውል በመግባቱ በየዓመቱ ብር 10,310.40 መክፈል እንዳለበት የውል ፎርሙ ተሞልቶ ውሉ መያዝ ሲገባው አሸናፊው ለካ.ሜ ባቀረበው የጨረታ ዋጋ ብር 1,611 በየዓመቱ እየተሰላ እንዲከፍል ተብሎ የሊዝ ውሉን ብር 8699.40 በማሳነስ ውል ተይዞ መገኘቱ፣

6.11 የጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተሞች ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ በሊዝ ቦታ ተሸጠው ለደንበኞች ባሸነፉበት ጠ/ዋጋ ውል መያዝ ሲገባ ውልን አሳንሶ በመያዝ ከ3 የጨረታ አሸናፊዎች ብር 1,405,000.00 ውል ሳያዝበት በከተማው በድምሩ ከውል በታች በማነስ ብር **2,158,203.40** ውል ተይዞ ተገኝቷል፡፡

**መ. ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ**

6.12 በ2007 በጀት ዓመት አንድ ተጫራች ለመኖሪያ አገልግሎት በጨረታ ቦታ ሲያገኙ የቦታ ስፋት 150 ካ.ሜ ፤ለካሬ ሜትር የተሞላው ዋጋ ብር 5001 የቦታው ጠቅላላ ዋጋ ብር 750,150 አሸንፊው ቅድሚያ ክፍያ ብር 75,015 ተቀንሶ ቀሪ ክፍያ ብር 675,135 ሲሆን ዓመታዊ ክፍያ ብር 13,502.70 በየዓመቱ ለ50 ዓመታት የሚከፈል ዉል መያዝ ሲገባው ብር 12,502.70 የሚከፈል ተብሎ ዉል ስለተያዘ ልዩነት 1000.00 ከዓመታዊ ክፍያ የሚቀር ሲሆን በ50 ዓመታት ብር **50,000** ሳይከፈል እንዲቀር የሚያደርግ ውል ተይዞ መገኘቱ፤

በአጠቃላይ በደብረ ማርቆስ፣ በደ/ታቦር፣ በጎንደር እና በባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤቶች በድምሩ በብር **4,565,138.89** የሊዝ ዋጋ አላግባብ ዝቅ ተደርጎ /በማነስ ውል ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ሁኔታውም ጨረታ አሸናፊው ባሸነፈበት ጠቅላላ ዋጋ ውል ባለመያዙ ከተማው ከመሬት ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በማሳጣት የከተማውን ህብረተሰብ የልማት ተጠቃሚነት በማዳከም የመልካም

አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ የአመታዊና ጠቅላላ የሊዝ ክፍን ዝቅ በማድረግ በኦዲት ባይደረስበት ያለፈው አመታትም ሆነ የቀጣይ ዘመናት የሊዝ ክፍያ ለግለሰቦች መጠቀሚያነት እንዲውል በር ከፍቷል፣ስለሆነም ውሉ በትክክለኛው መንገድ እንዲያዝና እስካሁን ያልተሰበሰበው ገንዘብ እንዲሰበሰብ ሆኖ ይህን የመንግስት ጥቅም ያሳጣ/ለማሳጣት የሞከረ እና ለግል ጥቅም እንዲውል ያመቻቸ አካል በህግ ሊጠየቅ እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

7. **በሊዝ ቦታ ተሸጦ ለገቢዎች ጽ/ቤት ባልተላለፉ የውል ሰነዶች ምክንያት ያልተሰበሰበ የሊዝ ሂሳብ በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡**

**ሀ. ደብረ ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት**

7.1 በ2010 በጀት ዓመት በ1ኛዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ ቦታ ለአንዲት ግለሰብ ሲሰጥ የቦታ ኮድ መ-1118 የቦታው ስፍት 150 ለካ.ሜ የተሞላው ዋጋ ብር 7001፣ ጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ ብር 1,050150.00 ተጫራቹ ባሸነፉበት ዋጋ ከጽ/ቤቱ ጋር ውል የተያዘ ቢሆንም የውል ሰነዱ ወደ አገልግሎቱ መዝ/ቤትና ገቢዎች ጽ/ቤት ሳይተላለፉ በፈጻሚው ጠረጴዛ ኪስ የተገኘ መሆኑ፣

**ለ. ጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ፤**

7.2 ከ2005-2010 ባሉት በጀት ዓመታት በግልፅ ጨረታ ለ341 ግለሰቦች መሬት በሊዝ በጨረታ ተሸጦ፤ነገር ግን የውል ሰነዱ ወደ ገቢዎች ጽ/ቤት ባለመተላለፉ ምክንያት በድምሩ ብር 5,856,002.76 ሳይሰበሰብ መገኘቱ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ሁኔታዉም መሰብሰብ ያለበት ገቢ ባለመሰብሰቡ መንግስት ማግኘት የሚገባው ገቢ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የከተማውን የመሰረተ ልማት፣የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችንና ልማትን በተሟላ ሁኔታ አለመፈፀምን አስከትሏል፡፡

7.3 **ውሉ ለሚመለከታቸው ቢተላለፍም የጉንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ** በ2005 እና 2007 በጀት ዓመት ለ10 የመኖሪያ ቤት ጨረታ አሸናፊዎች መሬት ከሊዝ ሽጦ በውል ሰነዱ መሰረት መመዝገብ የነበረበት የቦታ ጠ/ዋጋ ብር 4,384,550 ሲሆን በገቢ ማዕከሉ ተመዝገቦ የተገኘ ብር 1,851,944.50 ብቻ በመሆኑ በልዩነት ብር 2,532,605.50 በገቢ ማዕከሉ ባለመመዝገቡ በየዓመቱ እንዳይሰበሰብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁኔታው ለመንግስት ገንዘብ መባከንና ለሙስና በር መከፈቱ፣ ተገልጋዮችን ለምሬትና እንግልት የሚዳርግ እና በጽ/ቤቱ ላይ እምነት እንዲያጡ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ያለፈውም ሆነ ለወደፊቱ ትክክለኛው የውል ሰነድ ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስና በአግባቡ እንዲመዘገብ ሊደረግ እንደሚገባና ይህን በፈጸሙ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

**ለኦዲት ስራ ተፈልገው ሊቀርብ ያልቻሉ የሊዝ ፋይሎች በተመለከተ፤**

8. ለኦዲት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብና የመተባበርን አስፈላጊነት ጥፋትና ቅጣትን በተመለከተ የመ/ቤቱ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ማንኛውም ሰው ኦዲተሩ ለኦዲት ስራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ሰነዶች፣ የቃል ማስረጃዎች እና ወይም ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት የሚል ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

**ሀ. ጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ**

- የአጭር ጊዜ ሊዝ የተላለፉ የሰነድ ማስረጃዎችና ደንበኞች ፋይል፣
- የ2005 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 12,946,758.87 የያዘ 25 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ
- የ2007 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 20,265,804 የያዘ 49 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ
- የ2008 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር11,487,194.15 የያዘ 27 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 11,764,690 የያዘ 6 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ
- የ2009 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 682,650 የያዘ 1 የሊዝ ደንበኛ የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 2,235,000 የያዘ 3 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ
- የ2010 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 14,874,707.10 የያዘ 18 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 825,750 የያዘ 1 የሊዝ ደንበኛ የውል ሰነድ፤

በአጠቃላይ ብር **60,257,114.12** የያዘ 120 የመኖሪያ ቤትና ብር **14,825,440** የያዘ 10 የንግድ ድርጅት በጥቅሉ ብር **75,082,554.12** ብዛታቸው 130 የሊዝ ደንበኞች ውል ለኦዲት ስራ ተፈልገው እንዲቀርብ በተለያዩ ደብዳቤዎች በተደጋጋሚ ተጠይቆና ተፈልጎ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣

በዚህ ጉዳይ ላይ የጎንደር ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ፋይላቸው ያልተገኙ የሊዝ ሂሳብ ባለ ዕዳዎች መካከል 31 ያህሉ ብቻ እየከፈሉ መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን ሌሎቹ 99 ፋይሎችን ግን ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱ የማያውቃቸው መሆኑን ለመ/ቤታችን በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተጠቀሱት ፋይሎች መጥፋት ምክንያት የሆኑ አካላት በከተማ አስተዳደሩ እየተጣሩ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸውና ሰነዶቹ በትኩረት ተፈልገው እንዲገኙ ካልተገኙም የሊዝ ቦታቻዎቹና የደንበኞቹ ዝርዝር መሠረት በማድረግ በሊዝ በያዙት ቦታ ከላይ የተመለከተውን የሊዝ ዋጋ ውል መሠረት ባለዕዳዎች እንዲከፍሉ ክትትል ሊደረግባቸው እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡

**ለ. ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ፤**

- የአጭር ጊዜ ሊዝ የተላለፉ የሰነድ ማስረጃዎችና ደንበኞች ፋይል፣

- የ2005 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 9,754,686.00 የያዘ 12 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 191,744,028.00 የያዘ 15 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ
- የ2006 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር73,548,798.56 የያዘ 75 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ
- ድርጅት ብር 303,990,606.12 የያዘ 51 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ ፤
- የ2007 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 41,150,976.00የያዘ 27 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 313,502,839.00 የያዘ 15 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ፤
- የ2008ዓ.ም የመኖሪያቤት ብር 576,173,042 .21 የያዘ 26የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 1,988,818,505.25 የያዘ 25 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነ፤
- የ2009 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 266,922,037.00 የያዘ 18 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 113,854,599.75 የያዘ 7 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ፤
- የ2010 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ብር 415,863,695 የያዘ 15 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ የንግድ ድርጅት ብር 192,466,900 የያዘ 7 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ብር **1,383,413,234.77** የያዘ 173 የመኖሪያ ቤትና ብር **3,104,377,478.12** የያዘ 120 የንግድ ድርጅት በጥቅሉ ብር **4,487,790,712.89** ብዛት 293 የሊዝ ደንበኞች የውል ሰነድ ለኦዲት ስራ እንዲቀርብ በተለያየ ደብዳቤ በተደጋጋሚ ተጠይቆ በኦዲቱ ወቅት ተፈልጎ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት በደብዳቤ እና በቃል በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ይህ ሪፖርት ወጭ እስኪሆን ድረስ ምላሽ ሊሰጥ አልቻሉም፡፡

ለየቦታዎቹም ከአሸናፊዎቹ ጋር ውል ተይዞ የሊዝ ዋጋው ለከተማው እንዲከፈል ይረዳ ዘንድ ገቢዎች ጽ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ሁኔታውም መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያሳጣና የከተማውን ዕድገት የሚያጓትት በመሆኑ ድርጊቱን የፈፀሙ አካላት ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው የፍትህ አካላት አሳውቀናል፡፡

9. **አመታዊ የሊዝ ክፍያ ባለመከፈሉ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያና እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤**

9.1 የከተማ ቦታን በሊዝ ስለ መያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ዓ.ም አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የሊዝ ኪራይ ክፍያውን ለመክፈል በሚገባው የጊዜ ገደብ ዉስጥ በየዓመቱ ክፍያውን ባለመከፈሉ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው የሚሰጥ ሆኖ የ3 ዓመት ውዝፍ ካለበት ከ4ኛው ዓመት ጀምሮ አግባብ **ያለው አካል ንብረቱን ይዞ በመሸጥ ለውዝፍ እዳው መክፈያ ያውላል የሚል ቢሆንም** ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

**ሀ. ደብረ ማረቆስ ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮን/አገልግሎት ጽ/ቤት**

9.2 ከ2006-2010 ባሉ 5 በጀት ዓመታት በከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ላይ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ያልከፈሉት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው ሊሰጣቸዉ የሚገባ ከ1 እስከ 3 አመት የሆናቸዉ ደንበኞች

ብዛት 872 እና ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 8,505,818.25 እንዲሁም ቦታቸዉን ሊነጠቁ የሚገባ ከ4 እስከ 6 ዓመት የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 121 ሲሆን ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 3,150,091.62 በድምሩ **11,655,909.87** በጽ/ቤቱ ውዝፍ የሊዝ ተሰብሳቢ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

**ለ. በደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮን/ አገልግሎት ጽ/ቤት**

9.3 ከ2006-2010 ባሉ 5 በጀት ዓመታት በከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ላይ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ያልከፈሉት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው ሊሰጣቸዉ የሚገባ ከ1 እስከ 3 ዓመት የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 1114 እና ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 2,557,225.547 እንዲሁም ቦታቸዉን ሊነጠቁ የሚገባ ከ4-6 ዓመት የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 11 ሲሆን ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 130,469.05 በድምሩ **2,687,694.597** በጽ/ቤቱ ውዝፍ የሊዝ ተሰብሳቢ ሂሣብ የተገኘ መሆኑ፣

**ሐ. ጎንደር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ**

9.4 ከ1998-2010 ባሉ 12 በጀት ዓመታት በጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ላይ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ያልከፈሉት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው ሊሰጣቸዉ የሚገባ ከ1-3 ዓመት የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 865 ሲሆኑ ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 5,183,273.08 እንዲሁም ቦታቸዉን ሊነጠቁ የሚገባ ከ4 ዓመት በላይ የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 357 ሲሆን ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 7,637,090.19 በአጠቃላይ ወለድና ቅጣትን ሳይጨምር በድምሩ **12,820,363.27** በጽ/ቤቱ ውዝፍ የሊዝ ተሰብሳቢ ሂሣብ የተገኘ መሆኑ፣

**መ. ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መምሪያ**

**9.5** ከ1989-2011 ባሉ 22 በጀት ዓመታት በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ላይ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ያልከፈሉት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው ሊሰጣቸዉ የሚገባ ከ1-3 ዓመት የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 611 ሲሆኑ ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 51,196,697.61 እንዲሁም ቦታቸዉን ሊነጠቁ የሚገባ ከ4 ዓመት በላይ የሆናቸዉ ደንበኞች ብዛት 381 ሲሆን ያልተሰበሰበ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 57,609,364.41 በድምሩ **108,806,062.02** በጽ/ቤቱ ውዝፍ የተገኘ ሲሆን በአጠቃላይ በ4ቱ ከተማ አስተዳደሮች ብር **135,970,029.757** ውዝፍ የሊዝ ተሰብሳቢ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

ሁኔታውም በወቅቱ መሰብሰብ ያለበት የሊዝ ገቢ ባለመሰብሰቡ የመንግስት ገቢ ቀንሷል፡፡ እንዲሁም የከተማውን የመሰረተ ልማት፣የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዳይፈቱ አድርጓል፡፡ በሪፖርቱ ላይ ከየከተሞቹ ጋር በመሆን የማስተካከያ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑን ቢሮው ምላሽ እየሰጠ ይገኛል፡፡

II. በቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የስራ እድል ፈጠራ ዉጤታማነት፣የኮሌጆች ግንባታና ግብዓት አቅርቦት እና የሼድ ግንባታን የተመለከተ፤

10. ቢሮዉ ቅድመ ብድር ቁጠባ በራሳቸዉ ወይም በወላጆቻቸዉ ድጋፍ መቆጠብ ላልቻሉ ስራ ፈላጊዎች የካፒታል መፍጠሪያ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸዉ ሊያደርግ እንደሚገባ የኢንተርፕ ራይዞች ምስረታና ስራ እድል ፈጠራ የመሰረታዊ አመራር ለውጥ /የBPR/ ጥናት 2008 ዓ.ም ገጽ 15፣ 3.2 ተ.ቁ 14 ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

**በክልል ደረጃ**

10.1 በክልሉ በአብዛኞቹ ዞኖችና ከተሞች ቢሮዉ ከተቋቋመ ጀምሮ ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት 30/9/2011 ዓ.ም ድረስ በካፒታል መፍጠሪያ(ጥሪት ማፍሪያ)የስራ ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ በዉል ዘመናቸዉ መሰረት የቆይታ ጊዜያቸዉን ያጠናቀቁ ኢንተርፕራይዞች /ማህበራት/ ቢኖሩም የስራ ዘርፉን ያልተነጠቁ መሆኑና ለሌሎች የመቆጠብ አቅም ለሌላቸዉ ስራ ፈላጊዎች የማይተላለፍ መሆኑ፣

10.2 በጎንደር ከተማ አስተዳደር ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ለኦዲት አስከተደረሰበት ቀን 10/4/2011 ዓ.ም ድረስ በካፒታል መፍጠሪያ / ጥሪት ማፍሪያ / የስራ ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ በዉላቸዉ መሰረት የቆይታ ጊዜያቸዉን ያጠናቀቁ 16 ኢንተርፕራይዞች / ማህበራት / ቢኖሩም የስራ ዘርፉን ያልተነጠቁ መሆኑና ለሌሎች የመቆጠብ አቅም ለሌላቸዉ ስራ ፈላጊዎች ሳይተላለፍ መገኘቱ፣

10.3 በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ያልቻሉ ስራ ፈላጊዎችን በካፒታል መፍጠሪያ / ጥሪት ማፍሪያ / የስራ ዘርፎች ዉል እየያዙ እንዲሰማሩ ቢደረግም በዉሉ መሰረት የቆይታ ጊዜያቸዉን ሲያጠናቅቁ የያዙትን የስራ ዘርፍ እንዲለቁ በማድረግ ለሌሎች ስራ ፈላጊዎች እንዲተላለፍ እየተደረገ አለመሆኑና በዚህ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ስራ ፈላጊዎች ዉል የያዙበት መረጃም በዞን ደረጃም የሌላቸዉ መሆኑ፣

10.4 በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ከ2008-2011 ግምሽ በጀት ዓመት ድረስ በካፒታል መፍጠሪያ የስራ ዘርፎች ኮበል ማንጠፍና ማምረት ዉጭ በሌሎቹ (የደንና ደን ዉጤቶች ጥበቃ፣ የጫኝና አዉራጅ አገልግሎት፣የፓርኪንግ አገልግሎት፣የሌሊት መኪና ጥበቃ አገልግሎት፣የባጃጅ ተራ አገልግሎት ማስከበር፣ የመኪና እጥበት አገልግሎት፣የከተማ ጽዳት አገልግሎት፣ በመንግስት ተቋማት የመዝናኛ አገልግሎት እንዲሁም በመንገድ ዳር እና አካፋይ ሳር ተከላ አገልግሎት) ሃብቱ እያለና ስራ ፈላጊዎችን ስራ ላይ ማሰማራት እየተቻለ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ስራ ማስገባት ያልቻሉ መሆኑ ፣

ሁኔታዉ የመነሻ ካፒታል ለመበደር የሚያስስፈልጋቸውን የቅድመ ብድር ቁጠባ ለመቆጠብ አቅም ለሌላቸው ስራ ፈላጊዎች በተለይም ለዩኒቨርሲቲ፣ቴክኒክና ሙያ ምሩቃንና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች

ጉልበታቸውን ተጠቅመው ገቢ በሚያስገኙ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች በማስገባት በተቀመጠው የቆይታ የጊዜ ገደብ እንዲቆጥቡ በማድረግ ወደ ቋሚ የስራ መስኮች (የዕድገት ተኮር ዘርፎች) ለማሸጋገር እየተሰራ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል በዘርፉ የተሰማሩ ስራ ፈላጊዎችን በስራዉ ላይ በሚቆዩበት የዉል ዘመን ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ እንደ ቅድመ ብድር ቁጠባነት እንዲረዳቸው የማይደረግ መሆኑና ዉስን የሆነዉን ሃብት ለሌሎች ቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ላልቻሉ ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል አማራጭ እንዳይኖራቸዉ አድርጓል፡፡፡

## 11. ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠሪያ የመጣዉ ተዘዋዋሪ ብድር በተመለከተ፤

ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠሪያ የመጣዉ ተዘዋዋሪ ብድር ለወጣቶቹ ሊሰራጭና ለተፈለገዉ ዓላማ እንዲዉል ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንደሚገባ በክልሉ የወጣው የተዘዋዋሪ ብድር አጠቃቀም መመሪያ 2009 እና 2010 ዓ.ም ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ ተግባራዊ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

11.1 በጎንደር ከተማ አስተዳደር በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በ148 ኢንተርፕራይዞች ስር የተደራጁ 773 ስራ ፈላጊ ወጣቶች ብር 84,001,176 ብድር የወሰዱ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ 24 ኢንተርፕራይዞች ገንዘቡን ከወሰዱ በኋላ በጠየቁበት የስራ ዘርፍ በስራ ላይ ተሰማርተዉ የማይገኙ መሆኑና አንድ ኢንተርፕራይዝ ደግሞ ብር 900,000 ተበድሮ ሙሉ በሙሉ ቤት ገዝቶበት የተገኘ መሆኑ ፤

### ለ. ማዕከላዊ ጎንደር ዞን

11.2 በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በ2147 ኢንተርፕራይዞች ስር የተደራጁ 8,897 ስራ ፈላጊ ወጣቶች ብር 267,968,326.80 ብድር የወሰዱ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ 19 ኢንተርፕራይዞች ብር 3,382,457 ገንዘቡን ከወሰዱ በኋላ ብድሩን ከጠየቁበት የስራ ዘርፍ ዉጭ በስራ ላይ ተሰማርተዉ የሚገኙ መሆኑና 5 ኢንተርፕራይዞች ደግሞ ብድሩን ወስደዉ ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፣

### ሐ. እንጅባራ ከተማ አስተዳደር

11.3 በ2009 እና 2010 በጀት ዓመት የተዘዋዋሪ ብድር ለስራ ፈላጊዎች በሚሰጥበት ጊዜ ትክክለኛዉን የመመልመያ መስፈርት ጠብቆ ያለመመልመልና ስራ ፈላጊ ላልሆኑ ወጣቶች ብድር የተሰጣቸዉ መሆኑን ምላሽ የሰጡ መሆኑ፣

በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር በ2009 በጀት ዓመት በተዘዋዋሪ ብድር ለምትኩ ግዛትና ጓደኞቻቸዉ ብር 270,783 ለብሎኬት ማምረት የስራ ዘርፍ ብድር ቢወስዱም ገንዘቡን ከወሰዱ በኋላ በስራ ዘርፉ ላይ የማይገኙ መሆኑና የት እንዳሉም የማይታወቅ መሆኑ ፤

ሁኔታዉ ስራ ፈላጊ ኢንተርፕራይዞችና ግለሰቦች መጀመሪያ ላይ ካቀረቡት አዋጭ የቢዝነስ እቅድ ዉጭ ያልተጠናና አዋጭነቱ ባልተረጋገጠ የስራ ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ለኪሳራ እንዲዳረጉና የወሰዱትንም ብድር እንዳይከፍሉ እየዳረገ ያለ ተግባር ሆኗል፡፡ ስራ ፈላጊ ኢንተርፕራይዞችና ግለሰቦች

የወሰዱትን ብድር ባለመመለሳቸዉ ብድሩን በሚወስዱባቸዉ ከተሞች ላይ የብድር ዉዝፍ እንዲፈጠር በማድረግ ለከተማዎቹ ለተለያዩ የልማት አገልግሎት እንዲዉል ከሚመደብ በጀት ላይ ዉዝፉ እንዲከፍሉ የሚያደርግ በመሆኑ ከተሞቹን የተለያዩ የልማት አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ያደርጋል፡፡

**ለስራ እድል ፈጠራ የሚገነቡ ሸዶች ለስራ ፈላጊዎች (ኢንተርፕራይዞች) ስለማስተላለፍ፤**

12. በስራ እድል ፈጠራ የሚሰጡ በመንግስት የተገነቡ ሸዶች ለስራ ፈላጊዎች (ኢንተርፕራይዞች) ሲተላለፉ ዉል እየተያዘና በዉሉ መሰረት የቆይታ ጊዜያቸዉን ሲያጠናቅቁ እንዲመልሱ በማድረግ ለሌሎች ስራ ፈላጊዎች እንዲተላለፉ በማድረግ ለታለመለት ዓላማ እንዲዉሉ ሊደረግ እንደሚገባ በፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የመስሪያና መሸጫ ሼድና የገበያ ማዕከላት የቦታ ዝግጅት፣ ዲዛይን፣ ግንባታ እና አስተዳደር መመሪያ ላይ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ ተግባራዊ መሆኑን ኦዲት ሲደረግ ፡-

**ሀ. በክልል ቢሮ ደረጃ፤**

12.1 የክልሉ ቴ/ሙ/ኢ/ል/ቢሮ በ2006 ዓ.ም በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ 13 ከተሞች ለስራ ፈላጊዎች የመስሪያ ቦታ እንዲሆን ታስቦ 26 ሼዶችና 13 የመጸዳጃ ቤቶች በድምሩ 39 ፕሮጀክቶችን በተመሳሳይ ዲዛይንና ፕላን ሲያስገነባ የሚከተሉት ችግሮች ተስተዉለዋል፡-

- በ13ቱ ከተሞች የተካሄዱት 39 ፕሮጀክቶች ሲገነቡ ምንም አይነት ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ የአማራ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ አማካሪ (ተቆጣጣሪ መሃንዲስ) እና ግንባታዉን ገንቢ (ኮንትራክተር) ሆኖ እንዲገነባ በብር 142,105,792.02 የዉል ስምምነት ተወስዶ ግንባታዉ የተገነባ መሆኑ፣
- በግዥ መመሪያ ቁጥር 1/2003 በተቀመጠዉ አግባብ መሰረት የቅድመ ክፍያ የግንባታዉ የዉሉን 30% ከሚከፈለዉ ክፍያ ዉጭ ያሉት ሌሎች ክፍያዎች የሚከፈሉት የስራ ልኬታ ሰፍር /payment certificate/ እየቀረበና እየተገመገመ እንደሆነ ቢገልጽም የሁለተኛዉ ዙር ክፍያ ብር 36,394,353.41 ለአብክመ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ የተከፈለዉ ግን ምንም አይነት የስራ ልኬታ ሰፍር /payment certificate/ ሳይቀርብ የተከናወነ መሆኑ፣
- በክልሉ በ13 ከተሞች ለ39 ፕሮጀክቶች የተከፈለዉ ክፍያ ያልተጋነነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ከተገነቡት ሼዶችና ሽንት ቤቶች ዉስጥ በናሙና በዳንግላና በእንጅባራ ከተሞች የተገነቡትን በመምረጥ በአብክመ ከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ባለሙያዎች (መሃንዲሶች)

ግንባታዎቹ በተገነቡበት ወቅት (ዓመት) በነበረዉ የዋጋ መጠን መሰረት ዋጋውን እንዲያወጡ /እንዲገምቱት/ ሲደረግ፡-

1. **በዳንግላ ከተማ የተገነቡት 2 ሼዶችና 1 ሸንት ቤት** ቀደም ሲል የወጣላቸዉ ዋጋና ክፍያ የተፈጸመባቸዉ ብር 9,939,260.98 ሲሆን አሁን በኦዲቱ ወቅት በክልሉ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን መሃንዲሶች የተገመተዉ ዋጋ ደግሞ ብር 8,383,952.46 መሆኑና ልዩነት ብር 1,555,308.47 በብልጫ /ተጋኖ/ የተከፈለ መሆኑ ፣

➢ **በእንጅባራ ከተማ የተገነቡት 2 ሼዶችና** 1ሸንት ቤት ቀደም ሲል የወጣላቸዉ ዋጋና ክፍያ የተፈጸመባቸዉ ብር 9,695,394.99 ሲሆን አሁን በኦዲቱ ወቅት በክልሉ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን መሃንዲሶች የተገመተዉ ዋጋ ደግሞ ብር 8,488,327.74 መሆኑና ልዩነት ብር 1,207,067.24 በብልጫ /ተጋኖ/ የተከፈለ መሆኑ ፣

በሁለቱ ከተሞች በድምሩ ብር 2,762,375.71 የተጋነነ ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ በመሆኑ በቀሪዎች ፕሮጀክቶች ላይ በገለልተኛ ባለሙያዎች/መሃንዲሶች/ የዋጋ ግምቱ በስፋት ቢሰራ በተመሳሳይ ሁኔታ የተጋነነ የዋጋ ልዩነት ሊኖር የሚችል መሆኑ ታምኖበታል፡፡

12.2 ሁሉም (39) ግንባታዎች በ2006 ዓ.ም ተጠናቀዉ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአገልግሎት ዝግጁ የሆኑና የተወሰኑት ደግሞ አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም ግንባታዉን ያካሄደዉ የክልሉ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ እና የክልሉ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በህጋዊ መንገድ (በሰነድ ማስረጃ)ርክክብ ሳያካሂዱ የክልሉ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በጊዜያዊነት ግንባታዎቹን ተረክቦ አገልግሎት ላይ ያዋለ መሆኑ፣

➢ በዳንግላ ከተማ በ2006 በጀት ዓመት ለስራ ፈላጊዎች የመስሪያ ቦታ እንዲሆን ታስቦ በብር 9,939,260.89 በክልሉ ቴ/ሙ/ኢ/ል/ቢሮ አማካኝነት የተገነባዉ የክላስተር ሼድ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ቢሆንም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት 30/9/2011 ዓ.ም ድረስ ለ4 ዓመት ከ9 ወር በላይ ያለአገልግሎት ተዘግቶ የሚገኝ መሆኑ፣

➢ በ2006 ዓ.ም በሰቆጣ ከተማ ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል መፍጠሪያ እንዲሆን ታስቦ በክልሉ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በኩል በብር 10,077,304.23 የተገነባዉ ሼድ ለአንድ ባለሃብት ለቋንጣ ማድረቂያ አገልግሎት እንዲዉል በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በኩል የተሰጠ መሆኑና ኦዲቱ አስከተጠናቀቀበት ጊዜ 30/9/2011 ዓ.ም ድረስ ባለሃብቷ እየተገለገለችበት የሚገኝ መሆኑ፣

ለ.ጎንደር ከተማ አስተዳደር

12.3 በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ዉስጥ አልፎ አልፎ በመንግስት የተገነቡ ሼዶች ለስራ ፈላጊዎች ዉል እየተያዘ ከተሰጣቸዉ በኂላ በዉሉ መሰረት የቆይታ ጊዜያቸዉ ሲጠናቀቅ እንዲመልሱ በማድረግ ለሌሎች ስራ ፈላጊዎች የማይተላለፍ መሆኑ፣

ሐ. እንጅባራ ከተማ አስተዳደር

12.4 በእንጅበራ ከተማ አስተዳደር በ2010 በጀት ዓመት በ01 ማዕከል ስር በብር 385,353.17 ካስገነባው ለስራ ፈላጊዎች ያስተላለፋቸዉ 5 የስራ እድል መፍጠሪ ሼዶች ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 2/8/2011 ዓ.ም ያለአገልግሎት 1 ዓመት ከ6 ወር በላይ የተቀመጡ መሆኑና ለሌሎች ስራ ፈላጊዎች እንዲተላለፉ ያልተደረገ መሆኑ።

12.5 በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር እስከ 2011 ግማሽ በጀት ዓመት ድረስ በከተማዉ በተለያዩ ቦታዎች ለስራ እድል መፍጠሪያ እንዲሆን የኮንቴነር ማስቀመጫ ቦታ ለስራ ፈላጊ 17 ግለሰቦች ከተሰጣቸዉ በኂላ ኮንቴነሩን በመሸጥ ለሌሎች ግለሰቦች ያስተላለፉ መሆኑና በስራ እድል መፍጠሪያ አማካኝነት የወሰዱትን ቦታ እንዲያስረክቡና ለሌሎች ስራ ፈላጊ ዜጎች እንዲተላለፍ ያልተደረገ መሆኑ፣

12.6 በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር በ2010 በጀት ዓመት ለስራ እድል መፍጠሪያ ከገነባቸዉ 10 ሼዶች ዉስጥ 4ቱ ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 12/7/2011 ዓ.ም ድረስ ለ1 ዓመት ከ7 ወር ያህል አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ ፣

12.7 በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር በቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለስራ ፈላጊ ዜጎች ከተገነቡት የስራ እድል መፍጠሪያ ሼዶች ዉስጥ 22ቱን ስራ ፈላጊዎች ወስደዉ ያለአገልግሎት ዘግተዉ ያስቀመጧቸዉ መሆኑና 53 ሼዶችን ደግሞ ስራ ፈላጊዎቹ ስራ እየሰሩ ከስራ-አጥነት እንዲላቀቁ ቢሰጣቸዉም ለሌሎች ግለሰቦችና ነጋዴዎች አከራይተዉ የተገኙ መሆኑና ምንም አይነት የማስተካከያ እርምጃ በጽ/ቤቱ በኩል ያልተወሰደባቸዉ መሆኑ ፣

12.8 በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር በ01 ማዕከል ስር ከሚተዳደሩት 136 በመንግስት ከተገነቡ ሼዶች ውስጥ 135 ሼዶች ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ለስራ ፈላጊዎች የ1 ዓመት ውል እየተያዘ የተሰጣቸው ቢሆንም ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 14/8/2011 ዓ.ም ድረስ የውል እድሳት ሳያደርጉ በሼዶቹ ውስጥ እየሰሩበት ይገኛሉ፤

ሁኔታዉ በክልሉ በ13 ከተሞች የተገነቡት 39 ፕሮጀክቶች (26 ሼዶችና 13 ሸንት ቤቶች) ግንባታ በሚፈጸምበት ወቅት በዉድድር ሊገኝ የሚችልን አነስተኛ ዋጋ እንዳይገኝ በማድረግ በቀጥታ የግዥ ሂደት የተከናወነ በመሆኑ ለአብነት እንኳን በባለሙያዎች ተሰርተዉ ከተረጋገጡት የዳንግላና እንጅባራ ግንባታዎች ብር 2,762,397.71 ለተጋነነ ዋጋ ክፍያና ፍትሃዊ የጨረታ ውድድር መርህን የጣሰ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል በስራ ፈላጊነት የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር እያደገ በመምጣቱና ከአቅም ውስንነት የተነሳ ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልገውን የማምረቻና መሸጫ ቦታ ሙሉ በሙሉ ለማቅረብ የማይቻል በመሆኑ ያለውን ውስን ሃብትና አቅርቦት ከኢንተርፕራይዞቹ የስራ መስክና ቁጥር አንጻር እንዳይጣጣም አድርጓል፡፡ እንዲሁም ለስራ ፈላጊዎች የተገነባዉ ሼድ እንዲባክንና ተገቢ ላልሆነ ተግባር እየዋለ ሃብቱ ለሁሉም እንዳይዳረስና በቁጠባ እንዳይጠቀሙ አድርጓል፡፡

**የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የተበላሹ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች በማስጠገን የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን በተመለከተ፤**

13.በነባርና አዲስ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የተበላሹትን የማሰልጠኛ መሳሪያዎች በማስጠገን የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ እንደሚገባ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከ 2008-2012 ገጽ 78 እና የተቋማት ግንባታና ግብዓት የመሠረታዊ አሰራር ሂደት (BPR) 2008 ዓ.ም ጥናት ገጽ 10 ላይ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ተግባራዊ መደረጉን ኦዲት ሲደረግ፤

13.1 በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ 21 የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ዉስጥ ለተለያዩ የትምህርት ክፍሎች አገልግሎት የሚዉሉና ተጠግነዉ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸዉ 242 የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት ተቀምጠዉ የሚገኙ መሆኑና ከነዚህም ዉስጥ 92 የማሰልጠኛ መሳሪያዎቹ በብር 7,881,326.62 የተገዙ መሆኑ፣

**ሐ.ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

**13.2** በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ዉስጥ ካሉት 9 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ዉስጥ በሁለቱ (በንሃላ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ እና በአምባጊወርጊስ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ)ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 24/4/2011 ዓ.ም ድረስ በተገኘ መረጃ መሰረት 27 ዓይነት የማሰልጠኛ መሳሪያዎች የገጠማና ተከላ ስራዎች (ኢንስታሌሽን) ያልተሟላ በመሆኑ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፣

- በዞኑ ዉስጥ ከሚገኙት 9 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ዉስጥ በሁለቱ (በንሃላ እና በአምባጊወርጊስ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ) ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 24/4/2011 ዓ.ም ድረስ

ብዛታቸዉ 13 ዓይነት የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ተጠግነዉ አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በብልሽት ምክንያት ለ3 ዓመት ከ6 ወር ያህል አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣

**መ.እንጅባራ ከተማ አስተዳደር**

13.3 በእንጅባራ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ተጠግነዉ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት በብልሽት ምክንያት ተቀምጠዋል፡፡ (ለብረታ ብረት ምህንድስና ክፍል አገልግሎት የሚዉል (horizontal boring machine) ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት ምክንያት የቆመ፣ለጋርመንት ክፍል አገልግሎት የሚዉል (embordery machine)ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ ሁኔታዉ በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙ ላይ ሰልጣኝ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸዉን በተግባር የተደገፈ የክህሎት ስልጠና እንዳያገኙ አድርጓል፡፡ ቢሮው በሪፖርቱ መሠረት የማተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እየሰራ መሆኑን ገልጧል፡፡

III. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት፤

**በማዕቀፍ ግዥና ንብረት አወጋገድ ውጤታማነት ዙሪያን በተመለከተ፤**

**የእቃዎች ዝርዝር መግለጫ ቅድሚያ ጥናት የተደረገባቸውና በውሉ መሰረት ርክክብ ስለመደረጉ፣**

14. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣው ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2004ዓ.ም አንቀጽ 4 ገጽ 4 ተ.ቁ. 1 ላይ አገራዊ ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ያላቸዉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘዉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በተፈላጊዉ ጥራት እንዲያቀርቡ ያደርጋል የሚል ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

14.1 በተጠቃሚ መ/ቤቶች ተዘጋጅተው አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ እንዲፈጽምላቸው የሚላኩ የእቃ ናሙና እና ስፔስፊኬሽን ነበራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘቡና በገበያ ላይ የሌሉ መሆናቸው ለአብነትም፡-

- በ2009 በጀት አመት በመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ተዘጋጅተዉ አገልግሎቱ እንዲገዛቸው የተፈለጉ ባለ 5 በር ስቴሽን ዋገን መኪና የሚወጡ ዝርዝር ስፔሲፊኬሽን ሁሉንም አቅራቢዎች ያሳተፈ ሁኖ መዘጋጀት ሲኖርበት አንድን ተቋም/ሞይንኮን/ብቻ ትኩረት አድርጎ ዝርዝር ስፔስፊኬሽኖች ተዘጋጅተው መላካቸው እንዲሁም ከ60 እስከ 70 ኩንታል የሚጭን ገልባጭ የደረቅ ቆሻሻ ማንሻ መኪና ተብሎ መገለጽ ሲኖርበት የጭነት መኪና መገለጫ መቅረቡ፣ የአውቶሞቢል የመኪናው ከፍታ 150 ሚ.ሜትር ተብሎ መላክ ሲኖርበት 160 ሚ.ሚ ተብለው

በመላካቸው ሊገዙ የሚፈለጉ እቃዎችን መሰረት ያላደረጉና እቃዎቹን የማይገልጽ ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅተው በመላካቸው ሶስት ጊዜ ጨረታ እንዲወጣ ማስገደዱ፣

- በ2010 በጀት አመት አገልግሎቱ ለአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን 978 ሬንጀር ፊልድ ጃኬት በብር 3,574,844.00 ለመግዛት ከአልመዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ለመግዛት የባህርዳር ዩንቨርሲቲ አገልግሎቱ በመጀመሪያ ፖሊስ ኮሚሽን በላከው ስፔስፊኬሽን እና አቅራቢ ድርጅቱ ካቀረበው ናሙና ጋር አስመርምሮ ከሁኔዎች ጋር ተቀባይነት ያለው (conditionaly accepted) የሚል ውጤት በመስጠቱ አገልግሎቱ ከአቅራቢ ድርጅቱ ጋር ውል ይዞ እቃዎቹ ለፖሊስ ኮሚሽን ርክክብ ሊፈጽም ሲል ኮሚሽኑ መጀመሪያ የላከውን ስፔስፊኬሽን እና አቅራቢ ድርጅቱ ያቀረበው ምርት ግን በባህርዳር ዩንቨርሲቲ ሲመረመር ውጤቱ ውድቅ በመሆኑ ፖሊስ ኮሚሽን አልረከብም በማለቱ ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለበት ታህሳስ 4/2010 ዓ.ም ርክክብ መፈጸም የነበረበት ቢሆንም ይህ ኦዲት በአገልግሎቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ጥቅምት 30/2011 ዓ.ም ድረስ ለ11 ወራት በፖሊስ ኮሚሽን መጋዝን ውስጥ ታሽጎ አገልግሎት ሳይሰጥ ለጉዳት የተጋለጠ መሆኑ፣

14.2 በአገልግሎቱ ተዘጋጅተው ለቢሮዎች፣ ለዞንና ለሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች የማዕቀፍ ግዥ የተፈጸመባቸው የእቃዎች ዝርዝር መግለጫ (specification) ሲዘጋጁ ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች በትውስት እንዲዘጋጁ በመደረጉ እቃዎቹን በገበያ ላይ አለማግኘት፣ በተደጋጋሚ ጨረታዎች እንዲወጡ፣ ግዥዎች እንዲቀርቡ በተፈለገበት በጀት ዓመት ግዥ ሳይፈጸም እና አቅራቢዎቹ እንዲያቀርቡ ውል በያዙበት የእቃዎች መገለጫ የማይገዙ መኖራቸው፣ ለአብነትም፡-

- በ2007 በጀት አመት ከቪዥዋል ቴክ አስመጭ ድርጅት እና ኢካ ኮምፒውተር ኢንጅነሪንግ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአገልግሎቱ ጋር መካከለኛ ደረጃ አገልግሎት ሰጭ ላፕቶፕ (medium office purpose laptop computer 4th generation cor i5) መለያ ቁጥሩ ደግሞ **4210U** ተብሎ መዘጋጀት ሲገባው መለያ ቁጥሩ ደግሞ 3230m ተብሎ በ3ኛ generation ስፔስፊኬሽን ውል የተያዘ ሲሆን በርክክብ ወቅት አገልግሎቱ ችግሩ በቴክኒክ ግምገማ ወቅት የተፈጠረ ችግር በመሆኑ cor i5 4210U በሚል ርክክብ ሲፈጸም የሚፈለገው እቃ መገለጫዎች የጨረታ ሰነዶች ላይ በመዘጋጀቱ አቅሙ ያላቸውን ተጫራቾች ከውድድሩ የሚያርቅ እና የተወሰኑ ተጫራቾችን ብቻ እንዲጋብዝ ያደረገ መሆኑ፣
- በ2007 በጀት አመት ጁፒተር ትሬዲንግ ባሸነፈው የኮምፒውተር ግዥ ላይ Integrated wab camera ያለው ተብሎ ስፔስፊኬሽን ላይ ተቀምጦ አቅራቢ ድርጅቱ በርክክብ ወቅት Integrated wab camera የሌለው በማቅረቡ በተጠቃሚ መ/ቤቶች እና በአቅራቢ ድርጅቱ መካከል ርክክቡን አስቸጋሪ ያደረገና አገልግሎቱ ለዞኖቹ Integrated wab camera የሌለው በሚል ርክክብ ሲፈጸም

የሚፈለገው እቃ መገለጫዎች የጨረታ ሰነዶች ላይ በመዘጋጀቱ አቅሙ ያላቸውን ተጫራቾች ከውድድሩ የሚያርቅ እና የተወሰኑ ተጫራቾችን ብቻ እንዲጋብዝ ያደረገ መሆኑ፣

- በትራንስፖርት ቢሮ የተዘጋጁና አገልግሎቱ ከ2007-2010 በጀት አመት ለፈጸማቸው የተሽከርካሪ ጥገና ግዥ ላይ የወለልና የጣራ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው፣ በሁሉም ተሽከርካሪ አካል ላይ የማይገኙ እና በድግግሞሽ የተቀመጡ የጥገና አይነቶች መኖራቸው ለአብነትም፡- የፓምፕ ሰርቪስ፣ የካምቢዮ ሲሊንደር፣ ካሎ፣ የታፒሰሪና በትርኖ ስራዎች…የግንባር መስታወት መቀየር፣ የፊት እግር ዴስክ እና የኋላ እግር ታንቡር በቶርኖ መጠገን ያልተካተቱ፣ በድግግሞሽ የተካተቱ ደግሞ ሀብ ቤሪንግ፣ ነክል ቤሪንግ ለመቀየር (እግር ሰርቪስ ማድረግ)፤
- በ2009 በጀት አመት ለዞን ሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል 4840 ደስጣ ኮምፒውተር ወረቀት አዋሳ ከሚገኘው አማ ንግድ ድርጅት ግዥ ተፈጸሞ ለሴክተሮች የተከፋፈለ ቢሆንም ወረቀቱ በጣም የሳሳ እና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ 4 እስከ 7 ወረቀቶችን በአንድ ጊዜ ደራርቦ እያወጣና ከፕሪንተሮቹ ውስጥ እየተጠቀለለ እየቀረ ፕሪንተሮችን ለብልሽት የሚዳርግበት ሁኔታዎች መኖራቸው፣ ለአብነትም፡-
  - የኦዲት ቡድኑ ችግሩን በማዕ/ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያ ተገኝቶ በአካል ያረጋገጠ መሆኑ) በዚህ ጉዳይም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማኔጅመት አባላት በቀን 8/5/2011ዓ.ም ከዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ቡድን አባላት ጋር የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኃላ አገልግሎቱ በደብዳቤ በሰጠው ምላሽ የወረቀቱ የጥራት ደረጃ በቤተ ሙከራ አልተረጋገጠም የሚል ምላሽ የሰጡ ቢሆንም የወረቀቱን የጥራት ደረጃ አስቀድሞም ሆነ ችግሩ ከተያዘ በኃላ በቤተ ሙከራ የማረጋገጥ ኃላፊነት የራሱ በመሆኑ ተቀባይት የለውም፡፡

14.3 አገልግሎቱ በ2007 በጀት አመት ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በማዕቀፍ ግዥ የተፈጸመው “UPS” እቃዎች አገልግሎት የማይሰጡ ችግር ያለባቸው መኖራቸው ለአብነትም፡-

- የሰሜን ሸዋ ዞን ገ/ኢ/ት/መምሪያ በቁጥር ግዥ/ንብ/አስ/178/02/73 በቀን 22/12/2007 ዓ.ም የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አቅራቢ ለሆነው ሲማን ትሬዲንግ ካቀረባቸው ሰባቱ አገልግሎት የማይሰጡ ሲሆኑ (7*8600 UPS /ፓክ አፕ/ 1000VA basic purpos) እንዲቀየርላቸው በቁጥር ግዥ/ንብ/አስ/መ7/376/02/73 በቀን 10/01/2009 ዓ.ም ጠይቀው በአዲስ የተቀየረላቸው የኦዲት ቡድኑ በአካል ተዘዋውሮ ባያቸው 3 UPS ጠቅላላ ብር 25800.00 ዋጋ ያላቸው በሴቶችና ህጻናት 1፣ በግብርና መምሪያ 2 አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸውን በአካል ምልከታ የተረጋገጠ መሆኑ፣

14.4 ውጤቱም በአቅራቢ ድርጅቶችና በተጠቃሚ መ/ቤቶች መካከል አላስፈላጊ ጭቅጭቅና አለመጋባበቶች እንዲፈጠርና ንብረቶች ርክክብ ሳይፈጸምባቸው ያለ አገልግሎት እንዲቆዩ

አድርጓል፣ መ/ቤቶች በጠየቁት ፍላጎት መሰረት እቃዎችን አለማግኘታቸው በመልካም አስተዳደር ችግርነት መነሳት፣ ከስፔስፊኬሽኑ ውጭ የቀረበን ዕቃ ርክክብ ሳይፈጸምባቸው አገልግሎቱ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ የስራ ጫና ፈጥሯል፣ ግዥዎች ተቋርጠው መ/ቤቶች በጀታቸውን በወቅቱ ሳይጠቀሙበት እንዲቀር፣ የዋጋ ንረት፣ የጊዜ ብክነት፣ ለጉልበት ኪሳራና ጥራት የሌለው እቃ እንዲጠቀሙ አድርጓል፡፡

**ግዥዎች ከመከናዎናቸው በፊት ዋጋቸውና ገበያ ላይ ስለመኖራቸው መጠናቱን በተመለከተ፣**

15.በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2004ዓ.ም አንቀጽ 7 ገጽ 5 እና 6 (ሐ)ተ.ቁ 1 ለማንኛዉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብለት በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ዉስጥና የዓለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶች እንደሚሰጥ የሚገልጽ ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ችግሮች ተገኝተዋል፡፡

- በ2007 በጀት ዓመት ማፍ ኢንተርሽናል ድርጅት 375 ደስጣ የኮምፒውተር ወረቀት እንዲያቀርብ ውል ይዞ በውሉ መሰረት ባለማቅረቡ የሰ/ሸዋ ዞን ገ/ኢ/ት መምሪያ በቁጥር ግዥ/ንብ /አስ/30-1/3089/02/95 በቀን 24/10/2007ዓ.ም ለአገልግሎቱ ያሳወቀ ቢሆንም አቅራቢ ድርጅቱ እርምጃ ሣይወሰድበት እና በድጋሚ ያለፈው በጀት አመት የስራ አፈጻጸሙ ሳይገመገም ለ2008 በጀት ዓመት የጽ/መሳሪያና ፕሪንተር፣ ፋክስና ፎቶ ኮፒ ቀለም አሸናፊ ሁኖ እንዲቀርብ መደረጉ፣
- አገልግሎቱ በ2007 በጀት አመት የገዛው Medium office purpose /Samsung/ printer የአንዱ ፕሪንተር ዋጋ ብር 6,000 ሆኖ ፕሪንተሩ የሚጠቀመው LD 2035 ቀለም አንዱ ዋጋ ብር 5,247 የቀለሙ ዋጋ ከፕሪንተሩ ጋር የተቀራረበ በመሆኑ በበጀት አመቱ ቀለሙ እንዲገዛላቸው የጠየቁ ሴክተር መ/ቤቶች የቀለም ግገዡ አልተፈጸመም፣
- በ2007 በጀት አመት በከባቢያዊ ምድብ 3 ለጎንደር ከተማ አስ/ገ/ኢ/ት/መምሪያ ብዛት 20 ዩፒኤስ 750 ቪኤ ቤዚክ ኦፊስ ፕርፐዝ ለማቅረብ የቴክኒክ ግምገማውን አልፈው ለፋይናንሻል ወድድር ከቀረቡ ድርጅቶች መካከል ሲማን ድርጅት የአንዱ ዋጋ ብር 7,820.00 ሆኖ እያለ አገልግሎቱ አሸናፊ አድርጎ የለየው ኢካ ኮምፒውተር የአንዱ ዋጋ ብር 10,478.00 እና በከባቢያዊ ምድብ 1 ለክልል ቢሮዎች ብዛት 89 እንዲሁም በከባቢያዊ ምድብ 3 ለምዕ/ጎጃም ዞን/ገ/ኢ/ል/መምሪያ ብዛት 9 የአንዱ ዋጋ ብር 10,090.48 ብሪጅ ቴክ ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ያቀረቡ ድርጅቶች አሸናፊ በመሆን ዕቃውን እንዲያቀርቡ መደረጉ፣

- ሲማን የተባለው አቅራቢ ድርጅት ዩፒኤስ 750 ቪኤ ቤዚክ ኦፊስ ፐርፐዝ የቴክኒክ ግምገማውን አልፎ ለፋይናንሻል ውድድር እንዲቀርብ የተደረገ ቢሆንም በፋይናንሻል ውድድር ላይ ሲማን ያቀረበው ዋጋ በማወዳደሪያ ሰንጠረዡ ላይ ያልተካተተ እና ያለ ምንም ምክንያት ከውድድር ውጭ እንዲሆን በመደረጉ ኢካ የተባለ አቅራቢ ድርጅት በከባቢያዊ ምድብ ሶስት ለጎንደር ከተማ አስ/ገ/ኢ/ት/መምሪያ ብዛት 20x10478.00= 209,560.00 ብር ለማቅረብ ውል የወሰደ ሲሆን ሲማን የተባለው ድርጅት ያቀረበው የአንዱ ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር 7820.00x20=156,400.00 ብር ልዩነት ብር **53,160.00** እና
- በከባቢያዊ ምድብ 1 ለክልል ቢሮዎች ብዛት 89 እንዲሁም በከባባያዊ ምድብ ሶስት ለምዕ/ጎጃ ዞን/ገ/ኢ/ል/መምሪያ ብዛት 9 በድምሩ 98 የአንዱ ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር **10,090.48** ብሪጅ ቴክ በብር 988,867.04 ለማቅረብ ውል የወሰደ ሲሆን ሲማን የተባለው ድርጅት ያቀረበው የአንዱ ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር 7,820.00x98= **766,360.00** ልዩነት ብር **222,507.04** በአጠቃላይ ልዩነት ብር **275,667.04** ግዥው ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ሲማን ቢገዛ መንግስት ማግኘት የነበረበትን የዋጋ ቅናሽ ያሳጣ መሆኑ፣

ውጤቱም ተጠቃሚ መ/ቤቶች በአገልግሎቱ ላይ እምነት እንዳይኖሉ አድርጓል፤ የተመደበን በጀት በበጀት አመቱ እንዳይጠቀሙበት አድርጓል፤በዕቅድ ሊሰሩ የታሰቡ ስራዎችን በወቅቱ እንዳይ ፈጽሙና የተጋነነ ዋጋ ግዥንና ተጨማሪ ወጪን አስከትሏል፡፡

**ውል ከመግባቱ በፊት የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ማሳወቁን በተመለከተ፣**

16. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት ማስወገድ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 ገጽ 21 ተ.ቁ 17 ላይ ስለ ግዥው ምንነት ትክክለኛነትና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም እጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት እንዲቻል ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚገዟቸውን እቃዎች፣ የግንባታ ስራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህሪ የሚያሳይ የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት እንዳለባቸው የሚገልጽ ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ግኝቶች ተስተውለዋል፡፡
    - አገልግሎቱ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን ሊያስረክቡ የሚመጡ አቅራቢዎች በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ፣
    - አገልግሎቱ በማዕቀፍ የተገዙ እቃዎችን በውሉ ላይ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽንና ናሙና መሰረት በባለሙያ ተረጋግጠ መረከባቸውን የማረጋገጥ ስራ በዓመታዊ እቅድ በማካተት ያልሰራ መሆኑ፣

- አገልግሎቱ በሚፈጽማቸው የማዕቀፍ ግዥ ናሙና ለሚያስፈልጋቸውና ቴክኒካል ለሆኑ እቃዎች የዞን ባለሙያዎች ወደ ግዥ አገልግሎቱ ሲሄዱ ናሙና የለም ተብለው የሚመለሱበት፣ የአገልግሎቱ ባለሙዎች ወደ ዞኖች ወርደው በርክክብ ወቅት የማያረጋግጡና በንብረት ክፍል ውስጥ ናሙናዎቹ ሳይቀመጡ አገልግሎቱ አዘጋጅቶ በሚልከው ስፔስፊኬሽን ብቻ ታይቶ ርክክቡ የሚፈጸም መሆኑ፣
- አገልግሎቱ በ2007 በጀት ዓመት ለአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን የፖሊስ አባላት አገልግሎት የሚውል የደንብ ልብስ ግዥ ሲፈጽም አልማዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በድምሩ ብር 2,660,056.04 እንዲሁም ሲማን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር በጥቅሉ ብር 9,092,544.00 የደንብ ልብስ ለቴክኒክ ምርመራ ያቀረቡት ናሙና በባህርዳር ዩንቨርሲቲ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተፈትሾ ሳያልፉ/ተቀባይነት ሳያገኙ ድርጅቶቹ በቀጥታ ፋይናንሻል እንዲወዳደሩ ተደርገው ጨረታውን በማሸነፍ እቃዎችን እንዲያቀርቡ መደረጉ፣

ውጤቱም አገልግሎቱ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ናሙና አለመላኩ፣ተቋማትም ዕቃዎችን የተፈለገውን ጥራት ማሟላቱን በላብራቶሪ ወይንም በባለሙያ አረጋግጠው አለመረከባቸው እንዲሁም መንግስት ዕቃዎቹን ለመግዛት በሚያወጣው ገንዘብ ተመጣጣኙን ጥቅም እንዳያገኝ ማድረጉ፤ እቃዎች በሚፈለጉበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት በስፔስፊኬሽን መሰረት በትክክል ገቢ ስለመሆናቸው ክትትል አለማድረጉ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ሊቀርብላቸው የሚገቡ እቃዎችን በመጠባበቅ ስራቸውን በተቀላጠፈ መልኩ እንዳይሰሩ አድርጓቸዋል፣ እንዲሁም ሥራዎች እንዳይቋረጡ በሚል ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለተጨማሪ አላስፈላጊ ወጭ ዳርጓል፡፡

**ቅንጅታዊ አሰራርና የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ፣**

**የማዕቀፍ ግዥ ሰነዶች ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች መድረሳቸውን በተመለከተ፣**

17.በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2004ዓ.ም  አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7.2/ለ ገጽ 6 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ዉስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መ/ቤቶች እንዲያዉቁት ያደርጋል የሚል ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ችግሮች ተስተውሏል፡፡

17.1. አገልግሎት ለ48 የክልል መ/ቤቶች ከ2007-2010 ለ4 አመታት፣ለ10 ዞኖችና ለ3ቱ ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች ከ2007 እስከ 2009 ለሶስት አመታት በማዕቀፍ ለፈጸማቸው የእቃዎችና አገልገሎት ግዥዎች የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት፣ የጨረታ ሰነድ የተዘጋጀበት፣ የጨረታ ሂደቱን የሚገልጹ ቃለ ጉባኤዎች፣ አሸናፊው የተለየበት እና ከአሸናፊ

ድርጅቶች ጋር የተያዘውን የውል ስምምነት የሚገልጹ ሰነዶች ተጠቃለው ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በሙሉ ሳይላኩ አገልግሎቱ ላይ ብቻ የሚቀመጡ በመሆናቸው፡

ውጤቱም በርክክብ ወቅት በተጠቃሚ መ/ቤችና በአሸናፊ ድርጅቶች መካከል ከስፔስፊኬሽን ጋር ተያያዦ ለሚነሱ አለመግባባቶችን የጨረታውን ሰነድ ሌሎች ተያያዠ ሰነዶችን አይቶ ርክክብ ለመፈጸም የማያስችል መሆኑ፣ተጠቃሚ መ/ቤቶችንና አገልግሎቱን የጨረታ ሂደቱን የተወዳዳ ሪዎችን ሰነድ በሙሉ የሂሳብ ምርመራ አድርጎ ክፍያ ለመፈጸምና በፋይናንስ ህጉ መሠረት ለወጭው የተሟሉ ደጋፊ ሰነድ አለመኖርና ጠቅላላ አስተያየት መስጠት አለማስቻሉ፤

**የንብረት አወጋገድ ስርዓትን በተመለከተ፣**

**በመንግስት ተቋማትና በመ/ቤቶች ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች መወገዳቸውን በተመለከተ፣**

18. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንብረት አስተዳደር አዋጅና በዚሁ መሰረት በወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 34.5 እና 34.6 ማንኛውም በመጋዝን ወይም በግቢ ውስጥ ያለ ለመ/ቤቱ ጥቅም የማይሰጥ ንብረት ከአንድ በጀት አመት በላይ የመወገድ ውሳኔ ሳይሰጠው መቆየት የለበትም እንዲሁም መወገድ የሚገባው የመንግስት ንብረት እንዲወገድ ተጠይቆ ፈቃደኛ ባልሆኑ የንብረት ክምችትና ብልሽት እንዲፈጥር ምክንያት የሆኑ የበላይ አካላት፣ ሀላፊዎች፣ የስራ ሂደት ወይም ባለሙያ ለሚያደርሰው የመንግስት ንብረት ብልሽትና ያለአግባብ ለጥበቃ እና ለማከማቻ ለሚወጣ ወጭ ተጠያቂ ይሆናል የሚል ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

**ባለቤት የሌላቸው ተሽከርካሪዎችን፣ ልዩ ልዩ አይነት ብረታ ብረቶች እና የኤልክትሮኒክስ እቃዎች አወጋገድን በተመለከተ፤**

19. በ2008 በጀት አመት በደሴ ከተማ አስተዳደር በአገልግሎቱ በብር 2,000,000 ልዩ ልዩ ብረታ ብረቶች እንዲሸጡ ከተደረገ በኃላ በሌሎች ቦታዎች ከአምስት አመት ጀምሮ የተሰበሰቡ አገልግሎት የማይሰጡ ልዩ ልዩ ብረታ ብረቶች በሁሉም በክልል በሚገኙ ቢሮዎች፣ የዞን መምሪዎችና የወረዳ ጽ/ቤቶች የሚገኙ ቢሆንም ተሸጠው እየተወገዱና ወደ ገቢ እየተቀየሩ ባለመሆኑ በመ/ቤቶቹ ግቢ እና ንብረት ክፍል ውስጥ ክምችት ፈጥረው ለጉዳትና ለስርቆት ተጋልጠው የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ የጥበቃና አስተዳደር ወጭዎችን እያስከለተሉ መሆኑ፣ ለአብነትም፡-

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በቁጥር አብክ/ገ/ኢ/ል/ክቤ.01/20/8 በቀን 6/5/07ዓ.ም በክልል ደረጃ ለ44 ተቋማት እና ለ10ሩ የዞን መምሪያዎች በክልሉ የሚገኙ ማንኛውም አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ብረታ ብረቶችን ተቋማቱ ሳያስወግዱ በጥንቃቄ ተይዘው ወደ ፊት በክልሉ ለሚቋቋመው ለአማራ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ግብዓት እንዲሆኑ ታሳቢ እንዲደረግ ሰርኩላር ያስተላለፈ ሲሆን ከ3 አመት ተኩል በላይ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው እንደገና ቢሮው በደብዳቤ

ለአማራ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ በሁሉም የክልሉ ቦታዎች የተሰበሰቡ ብረታ ብረቶች ለስርቆት፣ በአያያዝ ጉድለት ለብልሽት እየተዳረጉና ከፍተኛ አስተዳደራዊ ወጭ እያስከተለ መሆኑን በመግለፁ አሁንም ንብረቶቹ ሙሉ በሙሉ እየተወገዱ አለመሆናቸው፣

19.1. በሁሉም የክልል ቢሮዎች፣ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች የሚገኙና ባለቤታቸው የማይታወቁ የመንግስት ተሽከርካሪዎች እየተወገዱና ገንዘቡ ለመንገስት ገቢ እተደረገ አለመሆኑ፣ ለአብነትም

- ክልል ቢሮ ላይ በአብክመ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር በቀድሞው የምዕራብ ጎጃም ዞን ግቢ ውስጥ አራት ባለቤታቸው የማይታወቁ ኮድ 4-00324 አማ ቲዮታ፣ ኮድ 4-00033 አማ ቲዮታ፣ ሰሌዳው ከላዩ የሌለ አንድ ስቴሽን ዋገን እና ኮድ 4-03948 አማ ሲኖትራክ መኪናዎች ከመቸ ጊዜ ጀምሮ እንደቆሙ የማይታወቁ ባለሙዎችን ጠይቅን በግምት ከአስራ ሁለት አመት በፊት ጀምሮ እንደሚያውቋቸው የገለጹልን ተሽከርካሪዎች አሁንም ይህ ኦዲት በአገልግሎቱ እስከተጠናቀቀበት ጥቅምት/2011ዓ.ም ሳይወገዱ ጉዳት እየደረሰባቸውና ሳር በቅሎባቸው የሚገኙ መሆናቸው፣
- በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በግብርና መመሪያ ጽል ግቢ ውስጥ ከመቸ ጊዜ ጀምሮ እንደተቀመጡ ባለቤታቸው የማይታወቁ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4- 00958 አማ እና 4- 00111 አማ ደብል ካፕ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣

**ከመ/ቤቶች አገልግሎት የማይሰጡና ያልተወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ፤**

19.2. በማዕከላዊ ጎንደር ዞን የመንግስት መ/ቤቶች ግቢ ውስጥ 6 አገልግሎት የማይሰጡ፣ ባለቤት እና የተሽከርካሪዎቹ ሙሉ መረጃዎች ያሏቸው ንብረቶች ሳይወገዱ ለጉዳት፣ ለብልሽትና ለብክነት ተዳርገው የሚገኙ መሆናቸው፣ ለመገለጫም፤

**በገጠር መንገድ ቢሮ በጎንደር ጥገና ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች፣**

19.3. መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎቹ እንደሚወገዱ በተሽከርካሪዎቹ ላይ የሚወገዱ የሚል ታግ የተለጠፈባቸው ሙሉ መረጃ ያላቸው 6 ገልባጭ፣ 2 ባለ ሁለት ጋቢና ቲዮታ፣ 1 ሎደር፣ 1 ግሬደር፣ እና 1 ትራክተር ተሽከርካሪዎች ሳይወገዱ ለጉዳት፣ ለብልሽትና ለብክነት ተዳርገው በግቢው ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው፣ በግቢው ውስጥ መወገድ እያለባቸው ያልተወገዱ 140 ከቀላል መኪና እስከ ከባድ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ ጎማዎች መኖራቸው፣

19.4. በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ግብርና ጽል ግቢ ውስጥ ንብረትነታቸው የጽሉ የሆኑ በቁጥር ከ8 በላይ የተለያዩ ተሽከርካሪና እና የተሽከርካሪ አካላት ተከማችተውና ለጉዳት ተጋልጠው የሚገኙ መሆናቸው፣

19.5. ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ንግድ ፑል በግቢው ውስጥ ንብረትነቱ የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ትራንስፖርት መምሪያ የሆነ ከአዘዞ ትራፊክ ኮምፕሌክስ ግንባታ ሲጠናቀቅ የተረፉና ያለ አገልግሎት የተቀመጡ 3 ጥቅል የኤሌክትሪክ ኬብል ገመድ የአንዱ ዋጋ ብር **23,614.25** የሆኑና ጠቅላላ በብር **70,842.69** የተገዙ ቢሸጡ በድምሩ ብር **120,432.57** ዋጋ ያላቸው ከ15/12/2007 ጀምሮ በግቢው ውስጥ ተቀምጠው ለጉዳት ተጋልጠው የሚገኙ መሆናቸው፣

19.6. በደባርቅ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ዋና ጽ/ቤት ወረዳው በቀን 21/07/2009 ዓ.ም ለማዕከላዊ ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መመሪያ በወረዳው በሚገኙ የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ መኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች እንዲወገዱ የገለጸ ቢሆንም ኦዲቱ በዞኑ እስከተጠናቀቀበት ነሃሴ19/2010 ድረስ ተሽከርካሪዎቹ ሳይወገዱ ጉዳት እየደረሰባቸው የሚገኙ መሆናቸው፣

**IV. የአማራ ክልል ቤቶች ልማት ድርጅት የቤቶች አስተዳደርና ህንፃ ግንባታን በተመለከተ፤**

**20. ድርጅቱ ከአከራያቸው የመኖሪያና የንግድ ቤቶች ወርሃዊ ኪራይና የሽያጭ ገቢ በአግባቡ እየሰበሰበ መሆኑን በተመለከተ፡-**

***በድርጅቱ የጎንደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤***

20.1. የድርጅቱን ቤት ተከራይተው የሚኖሩ በቁጥር **94** የሚሆኑ ተከራይ ግለሰቦችና እና ድርጅቶች **ከ2ወር እስከ 17 ዓመት** የሚደረስ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ውዝፍ ክፍያ በድምሩ ብር **1,593,481.85** በወቅቱ ድርጅቱ መሰብሰብ ሲገባው ይህ ኦዲት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እስከተጠናቀቀበት 30/09/2011 ዓ.ም ድረስ ሳይሰበሰብ የተገኘ መሆኑ፤

20.2. የጎንደር ቅ/ጽ/ቤት በቀበሌ 02 የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በ2009 ዓ.ም ለ22 ግለሰቦች ሲሸጥ የካሬ ሜትር ልዩነት በመፈጠሩ የገዙት ደንበኞች እንዲከፍሉ በደብዳቤ ድርጅቱ ያሳወቃቸው ቢሆንም የኦዲቱ ስራ እስከተጠናቀቀበት 30/09/2011 ዓ.ም ድረስ ብር **2,420,517.40** ድርጅቱ ከገዙት ደንበኞች መሰብሰብ ሲገባው ሳይሰበስብ የተገኘ መሆኑ፣

***ደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት***

20.3. የደሴ ቤቶች ልማት ድርጅት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 062 የሆነውን ጅ+4 አዲስ ህንፃ እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ13 ወር ኪራይ ብር 5,683,065.05፤ ቫትን ብር 852,459.75 እና ቅጣት 10% ብር 568,306.50 በድምሩ ብር **7,103,831.30** መሰብሰብ ሲገባው እስከ 24/05/2011 ዓ.ም ድረስ ሳይሰበሰብ የተገኘ መሆኑ፤

20.4. በደሴ ቅ/ጽ/ቤት የድርጅቱን ቤት ተከራይተው የሚኖሩ በቁጥር 17 የሚሆኑ ደንበኞች ከ2ወር እስከ 28 ወር የሚደረስ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ክፍያ በድምሩ ብር 297,896.73 በወቅቱ ድርጅቱ

መሰብሰብ ሲገባው ይህ ኦዲት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እስከተጠናቀቀበት 30/05/2011 ዓ.ም ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

ሁኔታውም ድርጅቱ በየወሩ የሚሰበስበውን የተለያዩ ገቢዎችን ሙሉ በሙሉ የማይሰበስብ ከሆነ በዕቅዱ ላይ እና በሚሰራው የስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፤የዋስትና መያዣ መጀመሪያ ላይ ቤቱን ሲከራዩ የ2 ወሩን የኪራይ መጠን ካላሲያዙ በተከራዩት ቤትም ሆነ ንብረት ላይ ጉዳት ቢደርስበት ለአፈፃፀም የሚያስቸግር መሆኑ እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ እንዲፈጥር የሚያደርግ መሆኑ፤

21. **ድርጅቱ የሚያስገነባቸውና የሚገነባቸው ግንባታዎች በተያዘላቸው የግንባታ ውል፤ጊዜ፤ ወጪና ጥራት አለመጠናቀቃቸውን በተመለከተ፡-**

21.1 በደሴ ከተማ እቴጌ መንን ት/ቤት አካባቢ ድርጅቱ ለሚያስገነባው **ጅ+9** ግንባታ አሸናፊው ድርጅት አልማኮን ህንፃ ተቋራጭ ሲሆን ተቋራጩ በገባው ውለታ መሰረት ቅናሽ /Rebate/ 3% በማለት የተወዳደረ ቢሆንም በየክፍያ ዙሩ ከሚቀርበው የክፍያ የምስክር ወረቀት ላይ 3% እየተቀነሰ ለተቋራጩ ክፍያ መፈፀም ሲገባው ይህ ሳይሆን በመቅረቱ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ከቫት በፊት ብር 8,205,925.62፤ የ2ኛ ዙር ብር 5,217,076.34 ፤ የ3ኛ ዙር እና የ4ኛ ዙር ክፍያ ብር 8,962,866.20 በድምሩ ብር 22,385,868.16 ለአልማኮን ስራ ተቋራጭ ወደ ተከፈተው የባንክ ቁጥር 2012111004774011 በባንክ ዝውውር ክፍያ ሲፈፀም (22,385,868.16*3%) ብር **671,576.05** አስቀድሞ የሰጠው ቅናሽ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፡፡

21.2 በደሴ ከተማ እቴጌ መንን ት/ቤት አካባቢ ለሚገነባው ጅ+9 ህንፃ ለአልማኮን ህንፃ ተቋራጭ የ5ኛ ዙር ክፍያ ሰነድ ተሰርቶ እስከሚቀርብ ድረስ በሚል በቀን 25/02/2009 ዓ.ም በድርጅቱ ሃላፊ በአቶ ሙሉየ አማረ በተሰጠ ትዕዛዝ ካለምንም የክፍያ ሰነድና ማስረጃ ብር 2,000,000.00 በባንክ ዝውውር ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤

21.3 በደሴ ከተማ እቴጌ መንን ት/ቤት አካባቢ ለሚገነባው ጅ+9 ህንፃ ከአልማኮን ህንፃ ተቋራጭ ጋር ከቀን 13/03/2007 ዓ.ም ጀምሮ በሃያ ወራት ውስጥ ስራውን አጠናቆ ሊያስረክብ በብር 57,362,719.23 ውል የተያዘ ቢሆንም እስከ 4ኛ ዙር ክፍያ ድረስ ቫትን ጨምሮ በድምሩ ብር 25,743,748.38 እና ከ5ኛ ዙር ክፍያ ታሳቢ የሚሆን በሚል ብር 2,000,000.00 በድምሩ ብር **27,743,748.38** ለተቋራጩ ተከፍሎ እያለ ለኮንትራክተሩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት መፍትሔ የማይገኝ ከሆነ ወደ ፍ/ቤት ጉዳዩን መውሰድ ሲገባ ግንባታው ሳያጠናቅቅ በስራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ስራው እንዲቋረጥ መደረጉ፤

21.4 በደሴ ከተማ እቴጌ መንን ት/ቤት አካባቢ ለሚገነባው ጅ+9 ህንፃ ከአልማኮን ህንፃ ተቋራጭ ጋር በቀን 13/03/2007 ዓ.ም በተደረገው የውል ስምምነት መሰረት የውሉን 20% ብር 11,472,543.85

ቅድሚያ ክፍያ በባንክ ዝውውር የተከፈለው ሲሆን እስከ 4ኛ ዙር ክፍያ ድረስ በድምሩ ብር 4,477,173.62 ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ በስራ የተመለሰ እና አጠቃላይ ግንባታውን አቋርጦ ለድርጅቱ ያስረከበ መሆኑ እየታወቀ እና አስቀድሞ ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ያልሰራበት ሂሣብ ለደርጅቱ መመለስ የነበረበት ቢሆንም በልዩነት ብር **6,995,370.23** የቅድሚያ ክፍያ ሳይመለስና በኮንትራክተሩ ላይ እርምጃ ሳይወሰድ ግንባታው ተቋርጦ የቀረ መሆኑ፤

21.5 በደሴ ከተማ እቴጌ መነን ት/ቤት አካባቢ በሚገነባው ጅ+9 ህንፃ ከአልማኮን ህንፃ ተቋራጭ ጋር በአማካሪ ድርጅቶች ወይም ባለሙያዎች የት ቦታ ላይ መሰራት እንዳለበት ጥናት ሳይደረግ በቁጥር ቤልድ/ሥ-769/07 በቀን 25/09/2007 ዓ.ም ተጨማሪ ውል በመያዝ ከህንፃው ጀርባ 1 ሜትር ከ20 ሳ.ሜ ርቀት **የድጋፍ ግንብ** ለማሰራት በሚል ብር 1,148,874.91 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን፤

- የተሰራው የድጋፍ ግንብ በአማካሪ ድርጅቶች ጥናት ተደርጎ ስራው ሙሉ በሙሉ ችግር ስላለበት እና ዋናውን ህንፃ ወድቆ ሊጎዳው በመሆኑ የተሰራው የድጋፍ ግንብ በባለሙያዎች ግምት መሰረት እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የድጋፍ ግንቡን ለማፍረስ ወጪ የሚጠይቅና ግንባታው ስህተት ያለበት መሆኑ በባለሙያዎች በጽሁፍ ተገልፆላቸው እያለ በኮንትራክተሩ ወጪ ማስፈረስና ማስተካከል እንዲሁም ይህን ትዕዛዝ የሰጠው /ውል የገባው/ አካል ተጠያቂ ማድረግ እየተገባ ኮንትራክተሩንም ሆነ ሌላ አካል ተጠያቂ ሳይደረግ ድርጅቱ ለብር 1,648,874.91 ተጨማሪ ወጭ መዳረጉ፣

21.6 ድርጅቱ በደሴ ከተማ ለሚገነባው ጅ+4 ህንፃ ለአትላስ ህንፃ ተቋራጭ አጠቃላይ የውሉን ብር 23,594,575.49 ላይ 20% ብር 4,718,915.098 ቅድሚያ ክፍያ በባንክ ዝውውር የተከፈለው ሲሆን እስከ 4ኛ ዙር ክፍያ ድረስ በድምሩ ብር 3,170,632.90 ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ላይ በስራ የተመለሰ እና አጠቃላይ ግንባታውን አቋርጦ በቀን 30/12/2009 ዓ.ም ለድርጅቱ ያስረከበ መሆኑ እየታወቀ አስቀድሞ ከተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ያልመለሰው/ያልሰራበት/ ለደርጀቱ መመለስ የነበረበት ቢሆንም በልዩነት ብር **1,737,824.76** የቅድሚያ ክፍያ ሳይቀነስ /ሳይመለስ ስራውን ባለበት አቋርጦ ለድርጅቱ 30/12/2009 ዓ.ም አስረክቦ ቢወጣም በድርጅቱ በኩል ክትትል ተደርጎ እንዲመለስ ያልተደረገ መሆኑ፤

21.7 ድርጅቱ በደሴ ከተማ ለሚገነባው **ጅ+4** ህንፃ ከአትላስ ህንፃ ተቋራጭ ጋር በቀን 16/05/2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 18/06/2007 ዓ.ም ድረስ ስራውን አጠናቆ ለማስረከብ በብር 23,594,575.49 ውል የተያዘ ቢሆንም እስከ 4ኛ ዙር ክፍያ ድረስ ቫትን ጨምሮ በድምሩ ብር **18,334,639.21** ተከፍሎ እያለ ለኮንትራክተሩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት መፍትሔ የማይገኝ ከሆነ ወደ ፍ/ቤት ጉዳዩን መውሰድ ሲገባ ግንባታው ሳያጠናቅቅ በስራአስኪያጁ ትዕዛዝ ስራው እንዲቋረጥ መደረጉ፣

21.8 ድርጅቱ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 15 ለሚገነባው ጅ+7 ህንፃ አጠቃላይ በብር 52,422,821.01 እያድ ኮንስትራክሽን ጨረታውን ያሸነፈ ሲሆን የውሉን 20% ብር 10,484,564.20 ቅድሚያ ክፍያ በተቋራጩ የባንክ ቁጥር 703C01003188 በባንክ ዝውውር ክፍያ የተከፈለው ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ብር 9,204,067.07 በባንክ ዝውውር ሲከፈለው ብር 1,840,813.41 ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ላይ የተቀነሰ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ክፍያ እንደጠየቀ ግንባታውን አቋርጦ ለድርጅቱ ያስረከበ መሆኑ እየታወቀ እና ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ የወሰደውን ለደርጀቱ መመለስ የነበረበት ቢሆንም በልዩነት ብር **8,643,750.79** የቅድሚያ ክፍያ ሳይቀነስ በቁጥር ቤልድ/ሥ-226/08 በቀን 09/03/2008 ዓ.ም የድርጅቱ ሃላፊ በነበሩት በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት በቀን 13/03/2008 ዓ.ም ስራውን ያስረከበ መሆኑ፤

ሁኔታው ድርጅቱ በወቅቱ ማግኘት ያለበትን ገቢ እና ጥቅም ያሳጣ መሆኑ፤የደሴ ጅ+4 እና ጅ+9 ህንፃዎች ያለበቂ ምክንያት ስራው በመቋረጣቸው በባለሙያ በተጠናው መሰረት ቀሪ ያልተሰሩ ስራዎችን ለማጠናቀቅ ከብር **42,121,092.87** በላይ ድርጅቱን ለተጨማሪ ወጪና ኪሳራ የዳረገው መሆኑ እንዲሁም ባህርዳር ቀበሌ 15 የሚገነባው ጅ+7 ህንፃ ተቋራጩ ግንባታውን ጀምሮ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ እንደተከፈለው ግንባታውን በማቋረጡ ድርጅቱን ለተጨማሪ ወጪና ኪሳራ የዳረገው መሆኑ፤

የደሴ ጅ+9 ህንፃ **የድጋፍ ግንብ** ስራው በጥናት በተረጋገጠው መሰረት የድጋፍ ግንቡ **ተገቢ ያልሆነና አደጋ የሚያደርስ** በመሆኑ በአዲስ ለተሰራበትና ለማስፈረሻ ተጨማሪ ወጪ ያስወጣው መሆኑና ለኪሳራ የዳረገው መሆኑ፤ በተጨማሪም ግንባታው የተጀመረው በ50/50 ቀመር በመሆኑ በደንበኞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ እና የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑ፤

## V. **የክልሉ ግብርና ቢሮ የሰብል ልማት፤ጥበቃና ቴክኖሎጅ አጠቃቀምና አፈፃፀም በተመለከተ፤ ለሰብል ልማት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች (ማዳበሪያና ምርጥ ዘር) በአይነት፣በመጠን እና በጊዜ መቅረባቸውን በተመለከተ፡-**

22. ቢሮው በአዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሰብል ልማት ግብዓቶች ጥራታቸው ተጠብቆ ለተጠቃሚዎች መሰራጨታቸውን መቆጣጠርና መከታተል እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተስተውለዋል፡

**ክልል ግብርና ቢሮ**

22.1. ከ2006/07 እስከ 2010/11 ምርት ዘመን ድረስ በክልሉ ውስጥ በየ ምርት ዘመኑ ከታቀደው **24,990,805** ኩ/ል ውስጥ **7,159,498 ኩ/ል (28.65 %)** የአፈር ማዳበሪያ እና ከ **2,084,485** ኩ/ል ውስጥ **1,344,931 (64.52 %) የምርጥ ዘር** አቅርቦት ሳይቀርብ መገኘቱ ፣

**በምዕራብ ጎጃም ዞን**

22.2.በ2010 /11 ምርት ዘመን የሰሜን አቸፈር ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ለምርት ዘመኑ

የማርየ መስራች ዘር ሽምብራ ለማባዛት ለ181.25 ሄ/ር መሬት 271.875 ኩ/ል ተጠይቆ ዘሩ ያልቀረበ መሆኑ፤

22.3. በ2010/11 ምርት ዘመን በሁሉም ሰብሎች የዘር ወቅት የግብዓት ችግር ያጋጠመ መሆኑ ለአብነት የቢራ ገብስ ምርጥ ዘር ዕቅድ 313 ኩ/ል ሲሆን 133(42.49%) ኩ/ል ያልቀረበ መሆኑ ፤

22.4. የገራይ ወንዝ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር ለ2010/11 ምርት ዘመን ለአካባቢ አርሶ አደሮች አገልግሎት የሚውል የሊሙ በቆሎ ምርጥ ዘር 200 ኩ/ል እንዲቀርብላቸው ቢጠይቁም 155 (77.5%) ኩ/ል ያልቀረበ መሆኑ፤

22.5. የገራይ ወንዝ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ለ2010/11 ምርት ዘመን 2,636.5 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ ብር 1,155 (2,636.5* 1,155 = ብር 3,045,157.5 ዩሪያ ማዳበሪያ ከመጋቢት እስከ ሚያዚያ ወር መቅረብ ሲገባው በዘር ወቅት ዘግይቶ ሐምሌ 2010 የቀረበ በመሆኑ በምርት ዘመኑ ሳይጠቀሙበት ለኦዲት እስከተደረሰበት 30/3/2011 ዓ.ም ድረስ ከ3 ወራት በላይ ከህብረት ስራ ማህበሩ መጋዝን ላይ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፤

22.6. በገራይ ወንዝ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ለ2009/10 ምርት ዘመን አገልግሎት የሚውል 480 ኩ/ል NPS ማዳበሪያ የአንዱ ዋጋ ብር 1,098 (480*1,098 = ብር 527,040.00 ከህብረት ስራ ማህበሩ መጋዝን ውስጥ እንደተከማቸ የዝናብ ፍሳሽ የተቀመጠውን ማዳበሪያ በማግኘቱ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ሳይውል ተበላሽቶ ያለ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ማረጋገጡ፣

22.7. በ2010 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ግብዓት በአይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በወቅቱ የቀረበ አለመሆኑ፤

- ዩሪያ (UREA) ከየካቲት እስከ ሚያዚያ ወር መቅረብ ሲገባው ዘግይቶ በሐምሌ ወር 2010 ገብቶ የተገኘ መሆኑ፤
- የቢኤች (BH) 661 ዝርያ ስርጸት ላይ ያለው የአመለካከት ችግር/የሚፈልጉትን የዘር ዓይነት እንዲቀርብላቸው ይህን አንፈልግም የሚል አስተሳሰብ / ያልተቀረፈ መሆኑ ፤
- የሊሙ በቆሎ ምርጥዘር እቅድ 8,470 ኩ/ል ሲሆን በምርት ዘመኑ የቀረበው በዞን ደረጃ 3,675 ኩ/ል ብቻ በመሆኑ በእጥረት 4,795(56.61%ሳይቀርብ የተገኘ መሆኑ ፤ ግብዓት የአካባበቢውን አግሮኢኮሎጅ መሰረት በማድረግ የማይቀረብ መሆኑ ፤ የሁሉን አውዳሚ ተምች ፍቱህ የሆነ ኬሚካል የማይቀረብ መሆኑ፤የዩሪያ ሳይድ ድሬሲንግ በወቅቱ አለማድረግና ሲያደርጉም ለትነት የሚጋለጥ መሆኑ፤

**ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ**

22.8. በ2010/11 ምርት ዘመን በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ውስጥ ባሉ ወረዳዎች በምዕራብ ደንቢያ 360 ሄ/ር፣ ምስራቅ ደንቢያ 1,598 ሄ/ር እና ጎንደር ዙሪያ 3127 ሄ/ር በድምሩ 5,085 ሄ/ር መሬት

የማሽላ ከሞዲቲ ስነ-ምህዳሩን መሰረት ያደረገ ምርጥ ዘር ማቅረብ ባለመቻሉ በአካባቢ ዘር ብቻ ተዘርቶ መገኘቱ ፣

22.9. ለጎንደር ዙሪያ ወረዳ የጭህራ ማንጠርኖ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ለ2010/11 ምርት ዘመን 4,689.5 ኩ/ል ዩሪያ ማዳበሪያ የካቲት 2010 እና 2,846 ኩ/ል ኤንፒየስ ማዳበሪያ መጋቢት 2010 ዓ.ም ጀምሮ በዘር ወቅት የቀረበ ቢሆንም 2,540.5 ኩ/ል ዩሪያ የአንዱ ዋጋ ብር 1,234.94 (2,540.5*1234.94 =ብር 3,137,365.07) እና 1,405.5 ኩ/ል ኤንፒየስ የአንዱ ዋጋ ብር 1,314.22(1,405.5*1,314.22=ብር 1,847,136.21 በድምሩ ብር **4,984,501.28** ወጭ የሆነበትን ማዳበሪያ በምርት ዘመኑ ሳይጠቀሙበት ለኦዲት እስከተደረሰበት 21/6/2011 ዓ.ም ድረስ ከህብረት ስራ ማህበሩ መጋዝን ላይ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ ፤

22.10. በጎንደር ዙሪያ ወረዳ የፀዳ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ለ2010/11 ምርት ዘመን 5,057 ኩ/ል ዩሪያ ማዳበሪያ እና 2,960 ኩ/ል ኤንፒየስ ማዳበሪያ በዘር ወቅት የቀረበ ቢሆንም 3,000 ኩ/ል ዩሪያ የአንዱ ዋጋ ብር 1,234.94 (3,000*1,234.94 = ብር 3,704,820 እና 1,500 ኩ/ል ኤንፒየስ የአንዱ ዋጋ ብር 1,314.22 (1,500*1,314.22 = ብር 1,971,330) በድምሩ **ብር 5,676,150** በምርት ዘመኑ ሳይጠቀሙበት ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 21/6/2011 ዓ.ም ድረስ ከህብረት ስራ ማህበሩ መጋዝን ላይ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ ተከማችተው የተገኙ መሆናቸውን ኦዲት ወቅት በተደረገ የአካል ምልከታ መረጋገጡ፣

***ውጤቱም*** የአፈር ማዳበሪያ በወቅቱ ባለማቅረብ የአርሶ አደሩን የዘር ወቅት ከማሳለፉ በላይ በምርት እድገት ላይ ተፅኖ መኖሩ፤ ምርጥ ዘር በአይነት፣ በመጠንና በወቅቱ በሁሉም አካባቢ ማቅረብ ባለመቻሉ በምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅኖ አሳድሯል፤ አርሶ አደሩ ግብዓት ባለበት ወረዳ ለመግዛት አላስፈላጊ ወጭ እንዲያወጣ አድርጓል፣ በዘር ለመሸፍን የታሰበውን ያክል ማሳ እንዳይሸፈን አድርጓል፣ በመጨረሻም አርሶ አደሩ ማግኘት የነበረበትን ምርት እንዳያገኝ አድርጓል።

**ሁሉም የቀረበ ምርጥ ዘር የመጠቀሚያ ጊዜው ሳያልፍ ጥቅም ላይ መዋላቸውን በተመለከተ ፤**

23. በየምርት ዘመኑ በአርሶ አደሩ ፍላጎት መሰረት የሚቀርቡ ምርጥ ዘሮች ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው ይታወቃል ። ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

23.1. በምዕራብ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው የምርጥ ዘር አይነቶች፡-

- በወምበርማና ሰከላ ወረዳዎች ከ2006/07 ምርት ዘመን ጀምሮ በቆሎ152.305 ኩ/ል የአንዱ ኩ/ል ዋጋ በብር 1,950 (1,950*152.305 = ብር 296,994.75 ፣
- በወምበርማ ወረዳ ስንዴ 575 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ በብር 1,400 (1,400 *575= ብር 805,000

- በሰከላ ወረዳ ከ2007/08 ምርት ዘመን ጀምሮ ጤፍ 38 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ በብር 2,300( 2,300*38 = ብር 87,400 እና
- በደጋዳሞት ወረዳ ገብስ 14 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ በብር 1,600(1,600* 14= 22,400) በድምሩ ብር **1,211,794.75** ወጭ የተደረገባቸው የምርጥ ዘር አይነቶች በተጠየቁበት ምርት ዘመን አገልግሎት ሳይሰጡ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው አልፎ መገኘቱ፣

23.2. በቡሬ ዙሪያ ወረዳ በ2008/2009 ምርት ዘመን ከቀረበው ምርጥ ዘር ውስጥ ሊሙ በቆሎ 329.125 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ ብር 5,300 (329.125*5,300=ብር 1,744,362.5 ፤ ሾኔ በቆሎ 82.375 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ ብር 4,560 (82.375* 4,560= ብር 375,630 እና ቀቀባ ስንዴ 129.5 ኩ/ል የአንዱ ዋጋ ብር 1,400 (129.5*1,400=ብር 181,300 በድምሩ ብር **2,301,292.5** በምርት ዘመኑ ሳይጠቀሙበት የቀሩና በነቀዝ የተጎዱ በዘር ብዜት ማህበራት መጋዝን ውስጥ ተከማችተው የአገልግሎት ጊዜያቸው አልፎ የተገኙ መሆኑ፡፡

***ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ***

23.3. ከ2006-2010 ምርት ዘመን ድረስ በማዕከላዊ ጎንደርና በስሩ ባሉ ወረዳዎች የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ ምርጥ ዘሮች ብር 2,640,378.2 እና ማዳበሪያ ብር 2,446,355.42 በድምሩ ብር 5,086,733.62 ወጪ የሆነባቸው ጥቅም ላይ ሳይውሉ በድምሩ ብር **5,086,733.62**

23.4. በ2006/07 እና 2007/08 ምርት ዘመን ለዘር አገልግሎት የሚውል አረርቲ የሺንብራ ዘር ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ዘር በድምሩ 187.5 ኩ/ል ብር 358,875 ሳይጠቀሙበት ተገኝቷል

***ውጤቱም*** በክልሉ ውስጥ የምርትና ምርታማነት ቀንሷል፣ አርሶ አደሮች ለኪሳራ እንዲጋለጡ አድርጓል፣ አንዳንድ ምርጥ ዘሮች በምርት ዘመኑ ሳይጠቀሙበት በየህብረት ስራ ማህበሩ የመጠቀሚያ ጊዜው አልፎ በመገኘቱ ክልሉ በምርጥ ዘር እራሱን እንዳይችል እጥረት አስከትሏል፡

**አርሶ አደሮች የግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚነትን በሁለተኛው የዕትዕ መነሻ ከነበረው 3% በ2009/10 በጀት አመት ወደ 18% የማደግ እቅድን በተመለከተ፡-**

24. የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጅን በስፋት በማቅረብ በ2009/10 ምርት ዘመን ወደ 18% ማሳደግ እንዳለበት የቢሮ ስትራቴጅክ እቅድ ገጽ 24 ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤-

**ክልል ግብርና ቢሮ**

24.1. የክልሉ ግብርና ሜካናይዜሽን /ትራክተር፣መወቂያ፣ኮባይነር/ አቅርቦት አናሳ በመሆኑና የተጠናከረ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ባለመሰራቱ በ2009/10 ምርት ዘመን በዕቅዱ መሰረት 18% መድረስ ሲገባው 6% ብቻ ሆኖ መገኘቱ፤

***ምዕራብ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ***

24.2. ለቡሬ ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል 52 የነፍስ ወከፍ ጤፍ መዝሪያ ከ2008

ዓ.ም ጀምሮ የአንዱ ዋጋ በብር 995.9 (52 * 995.9 = ብር 51,786.8 በወረዳው በጀት ተገዝቶ የጤፍ መዝሪያ ቴክኖሎጅውም ምንም ሙከራም ሳይደረግ እና ለአርሶ አደሩ ሳይሰራጭ ለ3 አመት ያህል ስቶር ክፍልን አጣቦ/አጨናንቆ መገኘቱ፣

24.3. ለቡሬ ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት አገልግሎት የሚሰጥ ባለ አራት እግር አንድ የጤፍ መስመር መዝሪያ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በብር 11,000 በወረዳው በጀት ተገዝቶ ምንም አገልግሎት ሳይሰጥ በብልሽት ኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 30/3/2011 ዓ.ም ድረስ ከ 4 ዓመት በላይ እስቶር ክፍል ውስጥ መገኘቱ፣

24.4. ባለቤትነታቸው የምዕራብ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ የሆኑ በጃቢጠህናን ወረዳ አጥር ግቢ ውስጥ 32 የጤፍ መስመር መዝሪያ የአንዱ ዋጋ 5,750 ( 32 * 5,750 = 184,000 ) ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 30/3/2011 ዓ.ም ድረስ ለ7 ዓመት ያህል በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጡ መገኘታቸው

24.5. ለጃቢጠህና ወረዳ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በAGP(Agriculture Growth Programe) እና ATA ተ.ቁ 22.8 (Agriculture Transformation Agency) በጀት ለወረዳው አምስት የበቆሎ መፈልፈያ ድጋፍ የተደረገ ቢሆንም ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ አራት የበቆሎ መፈልፈያዎች የአንዱ ዋጋ 56,000 ብር የሆነ (4*56,000 =224,000.00 ብር) አንድ በወረዳው ላይ የሚገኝ እና ሶስቱ (ማንኩሳ፣ ጅጋ እና አውንት) ቀበሌዎች የሚገኙት ሙከራ እንደተደረጉ ለ5 ዓመት ያህል መለዋወጫ የላቸውም በማለት ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 26/2/2011 ዓ.ም ድረስ ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ሁነው መገኘቱ ፣

24.6. ለቡሬ ዙሪያ ወረዳ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በወረዳው በጀት 5 ወኪንግ ትራክተር የአንዱ ዋጋ በብር 34,417.20 (5* 34,417.20 = በድምሩ 172,086.00 )ተገዝቶ ለወረዳው የቀረበ ቢሆንም ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 30/3/2011 ዓ.ም ድረስ ለ9 አመት ያህል አገልግሎት ሳይሰጥ በወረዳው ግብርና ጽ/ቤት አጥር ግቢ ውስጥ የተገኙ መሆኑ፤

24.7. ለቡሬ ዙሪያ ወረዳ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የግብርና ልማት ኘሮግራም (AGP) የግብርና ትራንስፎርሚሽን ኤጀንሲ (ATA) በጀት 3 የበቆሎ መፈልፈያ የአንዱ ዋጋ በብር 54,000 (3 * 54,000=ብር 162,000.00) ለወረዳው ድጋፍ የተደረገ ቢሆንም ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 30/3/2011 ዓ.ም ድረስ ለ7 ዓመት ያህል አገልግሎት ሳይሰጥ በወረዳው ግብርና ጽ/ቤት አጥር ግቢ ውስጥ የተገኙ መሆኑ፤

24.8. ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ለቡሬ ዙሪያ ወረዳና ለዞኑ እንደ ማዕከል ሆኖ በሙያና ቴክኒክ የተሰራው ቢቢኤም ማረሻ ብዛቱ 2,660 በብር 163 (163*2,660=ብር433,580.00) በዞኑ ውስጥ ላሉ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች እንዲሰራጭ የተሰራ ቢሆንም ለኦዲት እስከ ተደረሰበት ቀን 30/3/2011

ዓ.ም ድረስ ለ12 ዓመት ያህል ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ የግብርናን እስቶር ክፍልን አጣበ/አጨናንቆ መገኘቱ፣

**ማዕከላዊ ጎንደር ዞን**

24.9. በዞኑ የግብርና ልማት ጽ/ቤት የ2009/2010 ምርት ዘመን ነባሩን ቢቢም በአይባር ቢቤም መተካት አለመቻል አዲስ ለመግዛት ፍላጉት አለመፍጠር፤

- ➢ በዞኑ ውስጥ ለግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት ምቹ ቢሆንም ለተጠቃሚ አ/አደሮች የሚደረገው ግንዛቤ ፈጠራና አቅርቦቱን የማመቻቸት ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- ➢ አዲስ የቀረቡ ትራክተሮችን በግብአት አቅርቦት ና አጠቃቅም መመሪያን ተከትሎ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ፤

***ውጤቱም*** በክልሉ ውስጥ ያሉ አርሶ አደሮች የግብርና ሜካናይዜሽንን በ2009/10 በጀት አመት ወደ 18% ያላደገበት፡-ኮባይነር ሀርበስተርና የቁም መውቂያ ባለመሰብሰቡ በምርት ላይ የመጠንና የጥራት ጉድለት አምጥቷል ፣ መንግስት ከግብርናው /ከእርሻ/የተፈለገውን ያህል ገቢ እንዳያገኝ አድርጓል፤ምርትን በጥራት እንዳይመረት አድርጓል፣ ክልሉ የሚፈልገውን ያህል ምርትና ጥራት እንዳያገኝ አድርጓል፣ከተለመደው አሰራር ባለመውጣቱ ሰብሎች ለበሽታ፣ለነፍሳትና ተባይ እንዲጋለጡ ሁኗል፡፡

አጭር ጊዜ ተወስዶ ምርት እንዲመረት አልተቻለም፣አርሶ አደሩ እራሱንና ቤተሰቦቹን የሚመግብ አመታዊ የምግብ ፍጆታ በበቂ ሁኔታ እንዳያመርቱ አድርጓል፣ቴክኖሎጅን ባለመጠቀም የክልሉ አርሶ አደር ለበርካታ ሰዓት ጊዜውን በከንቱ እንዲያጠፋ ሁኗል ፣የተሰጠውን ምክረ ሃሳብ ባለመጠቀም ምርትና ምርታማነት መቀነስ እና የምርት ብክነትና የጥራት ችግር አስከትሏል፡፡

## VI. የክልሉ ትምህርት ቢሮ የኮሌጆች ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም፣የስልጠና ሂደት እና የሰልጣኞች ውጤታማነት የስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ፤

**የእጩ ሰልጣኞችን ምልመላ በተመለከተ፣**

25. በክልሉ ስር የሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሁሉም ፕሮግራም ሰልጣኞች ቅበላ የምልመላና መረጣ መመሪያውን መሰረት ተደርጎ በተሟላ መልኩ መሰራት እንዳለበት የትምህርት ቢሮው በ2009 ዓ.ም ያወጣው የእጩ ሰልጣኞች ምልመላ መመሪያ ይገልጻል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለፁት ግኝቶች ተስተውሏል፡-

25.1 በኮሌጆች የመግቢያ ፈተና ውጤታቸው ከ50% በታች ያመጡ ተማሪዎችን የሚቀበል (የሚመለምል) መሆኑ፡፡ለአብነት፡-

**በጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ**

- ➢ በ2011 ዓ.ም በማታው መርሃ ግብር ቅድመ መደበኛ ሰርተፊኬት ፕሮግራም ከ40 እስከ 49.9

ያመጡ 23 ሰልጣኞች፤ ዲፕሎማ ፕሮግራም ከ40 እስከ 49.6 ያመጡ 22 ሰልጣኞች፤ በልዩ ፍላጎት ከ32.7 እስከ 49.8 ያመጡ 21 ሰልጣኞች፤

- በ2007 ዓ.ም በመደበኛ መርሃ-ግብር በልዩ ፍላጎት ትምህርት ከ39.25 እስከ 49.8 ያመጡ 8 ሰልጣኞች፤
- በ2009 ዓ.ም በመደበኛ ፕሮግራም በሂሳብ ሊኒየር ትምህርት ከ36.5 እስከ 47.5 ያመጡ 4 ሰልጣኞች፤ አስቀድሞ ከወጣው የምልመላና መረጣ መስፍርትና አሰራር ውጭ ተመልምለው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

**በሬጅስትራር የስራ ክፍል የሰልጣኞችን መረጃ አያያዝ በተመለከተ፣**

25.2. በሬጅስትራር የስራ ክፍል የእያንዳዱ ተማሪ መረጃ በአግባቡ ተመዝግቦ ሊያዝና ዉጤት በወቅቱ /ቀጣዩ ሰሚስተር ከመጀመሩ በፊት/ ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተስተውለዋል፡፡

**ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ**

**25.3.** በሬጅስትራር የስራ ክፍል ተግባራት የሚከናወንበት የጊዜ ገደብ አስቀምጦ በመፈፀም በኩል ክፍተት መኖርና የተማሪዎችን ውጤት በወቅቱ አዘጋጅቶ አለመስጠት፡፡ ለአብነት፡-የማታ ተማሪዎችን የሁለተኛ ሰሚስተር ውጤት ከክረምቱ ጋር አብሮ የሚሰጥ መሆኑ፤ በሬጅስትራር የስራ ክፍል አድ እና ድሮፕ የሚያደርጉ ተማሪዎችን መረጃ ተለይቶ አለመያዝ እንዲሁም ፋይል የማድረግና ለተማሪዎች የማሳዎቅ ችግሮች ያለ መሆኑ፡፡

**ደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፤**

25.4. በሬጅስትራር የስራ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን ወይም ያመጡትን ውጤት ተቀይሮ የሚሞላ መሆኑ፡፡ለአብነት፡-

- የኮሌጁ የተማሪዎች ሪከርድ ባለሙያ በሆኑት አንድ ሠራተኛ መስከረም 7/2011 ዓ.ም ከተመረቁት ተማሪዎች ውስጥ የሰነ-ውበትና ሰውነት ማጎልመሻ የክረምት ተማሪ የሆነችው አንድ ተማሪ መታወቂያ ቁጥር HPGS/0050/06 የሆነ በአንድ ኮርስ ከዲ ወደ ቢ እና በሌላ ኮርስ ደግሞ ከሲ ወደ ቢ ተቀይሮ መመረቅ ሳይገባት እንድትመረቅ የተደረገ መሆኑ፤
- የኮሌጁ የተማሪዎች ሪከርድ ባለሙያ በሆኑት እኒሁ ሠራተኛ በሰኔ ወር 2010 ዓ.ም ከተመረቁት የሙዚቃ ትምህርት ክፍል የማታ መርሃ-ግብር ተማሪዎች ውስጥ አንዲት ተማሪ በመታወቂያ ቁጥር (IGSE/0130/08) ኮርሱን ያልሰራች ቢሆንም ኮርሱን እንደገና ሳትወስደው እንደወሰደችው ተደርጎ ሲ ውጤት ተሞልቶላት መመረቅ ሳይገባት እንድትመረቅ የተደረገ መሆኑ፤

➢ በሬጅስትራር የስራ ክፍል ውስጥ የሰልጣኞችን ውጤት በወቅቱ/ የሚቀጥለው ወሰነ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የማሳወቅ ችግር ያለ መሆኑ፡፡

***ውጤቱም*** *የተማሪዎች ውጤት በትክክል አለመመዝገብ፣መቀያየርና የውጤት መጥፋት ያስከተለ፤ መመረቅ የማይገባቸውን ተማሪዎች እንዲመረቁ ያደረገ፤መመዝገብ የማይገባቸው ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲገኙ ያደረገ፣ ተማሪዎችን ለእንግልትና መምህራን የውጤት ሪፖርት በተደጋጋሚ እንዲሰሩ ያደረገ፤ በክፍሉ ሰራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች መካከል እምነት ያሳጣ፤ ከስህተት የጸዳ መረጃ ለማዘጋጀት ያላስቻለ ነው፡፡*

**ለየመርሃ ግብሩ ተገቢነታቸዉ ተረጋግጦ የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎች /ሲለበሶችና ሞጁሎች/ መሰረት እያንዳንዱ ኮርስ በአግባቡ እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ፣**

26. በክልሉ በሚገኙ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ለየመርሃ ግብሩ ተገቢነታቸዉ ተረጋግጦ የተዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎች /ሲለበሶችና ሞጁሎች/መሰረት እያንዳንዱ ኮርስ በአግባቡ እየተሰጠ መሆኑን እየተገመገመ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የት/ቢሮ የካቲት ወር 2009 ዓ.ም ባወጣው ኢንስፔክሽን ስታንደርድ ገጽ 10 ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ይህን ለመገምገም ኦዲት ሲደረግ የሚከተለው ተስተውሏል፡

**ደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ**

26.1. በኮሌጁ ተማሪዎች መወሰድ የማይገባቸውን ኮርሶች የሚወስዱ እና መወሰድ የሚገባቸውን ኮርሶች የማይወስዱ መሆኑ፡፡ ለአብነት፡-

➢ በ2007 ዓ.ም ለጅኦግራፊ ሰልጣኞች መሰጠት የሌለበት ቋንቋ መሠረታዊ ኢንግሊሽ (Basic English I (ENG.110) ኮርስ ተተክሎ የተሰጠ መሆኑ፤

➢ ከአሰልጣኝ መምህራኖች ውስጥ እለታዊ የትምህርት እቅድ በተሟላ መልኩ የማያዘጋጁ እና እለታዊ የትምህርት እቅድ ሳያዘጋጁ የሚያስተምሩ መምህራን መኖራቸው፡፡

**በጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ**

26.2. በኮሌጁ ለተማሪዎች መሰጠት የማይገባቸው ኮርስ በስህተት የሚሰጣቸው መሆኑና ቀድመው መውሰድ ሚገባቸውን ኮርሶች የማይወስዱ መሆኑ፡፡ለአብነት፡-

➢ በ2009 ዓ.ም 1ኛ አመት የአርት የማታ ተማሪዎች የተመዘገቡት ኮርስ MT-101 ሁኖ እያለ የተማሩት ግን MT-112 በመሆኑ ተማሪዎች ቀድመው መውሰድ የሚገባቸውን ኮርስ እንዳይወስዱ ያደረገው አሰራር መሆኑ፤

➢ በ2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ሰርተፊኬት ተማሪዎች የቅድመ ኢንግሊዝኛ (Pre-Eng-101) ኮርስ መውሰድ ሲገባቸው መምህሩ በስህተት ለዲፕሎማ የሚሰጠውን ኮርስ እንግሊዝኛ (Eng-

101) ሲያስተምር የተገኘ በመሆኑ የአጋማሽ ፈተና ጊዜ ለአንድ ሳምንት ተራዝሞ መምህሩ እንደገና እንዲያስተምር የተደረገ መሆኑ፤

27. ***ውጤቱም*** ለሰልጣኞች የሚሰጡ ኮርሶች ሳይሸፈኑ እንዲቀሩ ያደረገ፣ ሰልጣኞች ማግኘት የሚገባቸውን እውቀት እንዳያገኙ ተጽዕኖ የፈጠረና የትምህርት ጥራትን የሚቀንስ ነው፡፡

## VII. የአማራ ክልል የጤና ጥ/ ቢሮ የእናቶችና ህፃናት የጤና አገልግሎት አሰጣጥን፤

**28. በገጠር እና በከተማ በሚገኙ ጤና ኬላዎችና ጤና ጣቢያዎች የእናቶች ጤና አገልግሎት ተግባርን ለማከናዎን የሚያስችሉ የህክምና ቁሳቁሶች በሚፈለጉት አይነትና ብዛት ተሟልቶ እየቀረበ መሆኑን በተመለከተ፤**

**በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ**

28.1. በ2008 በጀት አመት **የጎ/ዙ/ወ/ጤ/ጥበቃ ጽ/ቤት** የ1ኛው ዙር ወይም የ25% መድሀኒት አቅራቢ ኤጀንሲ /PFSA/ እንዲያቀርብለት ቢጠይቅም አቅራቢው ማቅረብ ያልቻለ ተብለው ከተገለጹት መድሀኒቶች መካከል ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ወቅት ወይም ከወሊድ በኃላ የእናቶችን ጤና ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ የተለያዩ መድሃኒቶች(Cloxacilin 500g capsule፤Antacid suspension፣ Ampicilin injction እና Magnesuium sulfate injection)፣

28.2. **በደባርቅ ወ/ጤ/ጥ/ጽ/ቤት** የ2ኛ ዙር የተለያዩ የአርዲኤፍ (RDF(50%) **መድሀኒት** (Jemsa stain solution፣ Erytromycine 250mg፣ Gentamycine eye drop፤Water for inj፤Hyocine 10mg tablet፤ Sulbutamole inhalation፤ HCG፤ CAF eye drop፤Wiel flex) **ተጠይቀው ያልቀረቡ መሆኑ እና**

28.3. **በወገራ ወረዳ ጤና ጥበቃ** ጽ/ቤት የሁለተኛ ዙር የአርዲኤፍ (RDF) **መድኃኒቶች ተጠይቀው ከመጡት ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዚያቸው** ከ3 ወር **በታች ሆኖ የመጡ መድሀኒቶች** (Water for injection 10ml–70 እናRPR carbon—8) ፤

28.4. **በጣቁሳ ወረዳ** ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የተለያዩ መድሃኒቶች (Surgical glove 7.5፣ Anti A-Monoclonal፤Anti B-Monoclonal፤Anti D-Monoclonal፤Emtronmcin 250 mg lcapsv፤ Hydrocertisone Acetatecrca፤Cotrimoxuzole 48mgta) **ተጠይቀው ያልቀረቡ መሆኑ፣**

28.5. በመድኃኒት ፈንድ ኤጀንሲ ጎንደር ቅርንጫፍ በኩል የፕሮግራም መድኃኒቶች በየሁለት ወሩ በቀጥታ ስርጭት የማይደርስባቸዉ ጤና ጣቢያዎች (በደባርቅ ዙሪያ ድብ ባህር እና አርገንጅ፣

በአለፋ አፀደ ማሪም፣ ደንቢያ አበርጅሃ፣ በጣቁሳ ድኩላርባ፣ በመተማ መቃ፣ በቋራ ዱባባ፣ በመዕ/ በለሳ ወረሃላ፣ በጎን/ዙሪያ ምንዝሮ፣ በላይ አርማጭሆ ሙሴ ባንብ እና ጭራ አምብዞ) መሆናቸው፤

28.6. በ2010 በጀት **የሳንጃ** የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በምግብ እጥረት የተጎዱ ህፃናትን ለማከም ሙሉ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን የገለጸ ቢሆንም የህክምና ግብዓቶች በሆስፒታሉ ሆነ በወረዳዉ ባለመኖሩ ችግሩ እንዲፈታለት በቀን 09/11/10ዓ.ም ለዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ ቢገልጽም ችግሩ ኦዲቱ እስከደረሰበት ድረስ ያልተቀረፉ መሆኑ፣

28.7. በ2011 በጀት አመት **በምዕራብ ደንቢያ ወረዳ** ጤ/ጥ/ጽ/ቤት ስር የሚገኙ በአራት( ጫኺት ፣ሳንኪሳ፣ አብርሃጅራ እና አባዉራም)ጤና ጣቢያዎች ላይ የአንደኛዉ ዙር እንዲቀርብለት ከጠየቃቸዉ 248 መድኃኒቶች ውስጥ 126ቱ ያልቀረቡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 31 የሚሆኑት vaital (በጤና ተቋማት መጥፋት የሌለባቸው) እና 90 የሚሆኑት ደግሞ አስፈላጊ (essential ቢሆኑም እንዳልቀረቡ የታወቀ ሲሆን በተመሳሳይ የምዕራብ በለሳ ወረዳ ጤ/ጥ/ጽ/ቤት በአንደኛዉ ዙር ተጠይቀው ያልመጡ 24 መድሀኒትና በወርሀላ ጤና ጣቢያ 5 የሚሆኑ መድሀኒት በተጠየቀው ጊዜ ያልቀረቡ መሆናቸው፤

28.8. በ2010 በጀት አመት **የአይከል** ጤና ጣቢያ በቁጥር መ1/1/202 በቀን 29/03/2010 **የግብአት ስርጭትን** አስመልክቶ በግብረ መልሱ ለመድሀኒት ፍንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደገለጸው ኤጀሲው በጎንደር ቅርንጫፍ በኩል የመድሀኒትና የህክምና መገልገያዎችን በየሁለት ወሩ በሚልከው (RRF) የፕሮግራም መድሀኒቶችን ስርጭት የሚያቀርብ መሆኑን የሚታወቅ ቢሆንም፤

ኤጀንሲው የ(RRF)ፕሮግራም መድሀኒቶችን እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ የተፈለገውን የመድሀኒት መጠን ሙሉን ማቅረብ እንዳልቻለና ከተጠየቁትም መድሀኒቶች ውስጥ ጭራሹን የማያቀርብበት ሁኔታ እንዳለ እና በየአመቱ እንዲያቀርብ ከሚጠየቀው መጠንም እየቀነሰ (እያሽቆለቆለ) የሚገኝ ሲሆን ተቋማት መድሀኒቱን ከአቅራቢው ድርጂት ላይ ባለማግኘታቸው በከፍተኛ የዋጋ መጠን በክልሉ ውስጥ በጅምላ እንዲያከፋፍሉ ፍቃድ ከተሰጣቸው የግል ተቋማቶች ላይ ለመግዛት እንደሚገደዱና መድሀኒቱን ለሚጠቀሙ ግለሰቦች (ህሙማን) በወቅቱ ለመጠቀም የማይደርስላቸው መሆኑ፤

28.9. በ2008 በጀት አመት መምሪያው ለክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በቁጥር ሰጎጤ2/19/3053 በቀን 12/8/2008 በተጻፈ ደብዳቤ **የማዋለጃ አልጋን** አስመልክቶ በዞኑ ውስጥ ባሉ ጤና ድርጂቶች

አገልግሎት የሚውል የማዋለጃ አልጋ ፍላጎት በ22 ወረዳዎች በድምሩ187 አልጋ እንደሚያስፈልግ የገለጸ ቢሆንም ችግሩ ለኦዲት እስከ ተደረሰበት ግንቦት 2011 በሚፈለገው ተሟልቶ የተቀረፈ አለመሆኑን እና ቢያንስ በአንድ ጤና ጣቢያ እና ጤና ኬላ አንድ አልጋ ብቻ ሊኖር እንደሚችል እና ይህም ሁለት እና ከዚያ በላይ ለወሊድ አገልግሎት የሚመጡ ወላድ እናቶችን በተመሳሳይ ሰአት ለማስተናገድ ችግር ያለ መሆኑ፤

28.10. በ2011 በጀት አመት **የማክሰኝት** ጤና ጣቢያ በቁጥር ማጤጣ 398/21/011 በቀን 16/1/2011 **ለደንቢያ ሆስፒታል** የባለሙያ ትብብርን አስመልክቶ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደተገለጸው ሆስፒታሉ የባዮሜዲካል ቴክኒሻል ባለሙያ ያለው በመሆኑና በማክሰኝት ጤና ጣቢያ ባለሙያ ያልተመደበ በመሆኑ ከ22/1/2011 ጀምሮ በትስስሩ መሰረት ባለሙያው ከሚሰራበት ሆስፒታል በተጨማሪ በጤና ጣቢያው እንድትወክሉልን በማለት የጠየቀ ሲሆን በጤና ጣቢያ አንድ የባዮሜዲካል ባለሙያ መኖር የሚገባው ቢሆንም በተመሳሳይ በሌሎች ጤናጣቢያዎች የተጠየቀው ባለሙያ የሌላቸው መሆኑ፤

28.11. በ2008 በጀት አመት **የደንቢያ** ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በቁጥር ደጤ/555/08 በቀን 15/11/2008 ለአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ **የሰረጂካል ግላቭ** ለእናቶች የወሊድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በወረዳው ውስጥ የሌለ በመሆኑ በማለት ለክልሉና በግልባጩ ለመምሪያው እንዳሳወቀው ወረዳው የእናቶችን የወሊድ አገልግሎት ለመስጠት ችግር የገጠመው ቢሆንም ኦዲቱ እስከደረሰበት ድረስ የሰረጂካል ግላቭ እጥረት በሁሉም ወረዳች ላይ እንደሚከሰትም የኦዲት ማስረጃዎች ማረጋገጣቸው፡፡

28.12. በ2011 በጀት አመት በዞኑ **የማቀዝቀዣ (ፍርጂን)** በዞኑ ውስጥ በወረዳዋች፣ በጤና ጣቢያዋች እና በጤና ኬላዋች እንዲሁም በሆስፒታሎች አገልግሎት የማይሰጡና የሌላቸውን በተመለከተ፡ የሌላቸው ሆስፒታሎች-(ጭልጋ ቁጥር1 እና ጠገዴ) ሲሆኑ በ14 ወረዳዎች ማቀዝቀዣ የሌላቸው ጤና ኬላዎች ብዛት 211 እንደሆኑና በኤሌክትሪክ ብቻ የሚሰሩ ማቀዝቀዣዎች የተለየ ብዛት ሞዴል (304mk ብዛት 8,408mk ብዛት 2, tcw3000 ብዛት 57,tcw2000 ብዛት 2,tfw800 ብዛት 3 በጠቅላላው 72፣.በኪሮሲንና በኤሌክትሪክ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ማቀዝቀዣ የተለያዩ ሞዴልና ብዛት ያላቸው (rcw50 ብዛት 121፤ sivir110 ብዛት 50፤ sivir170 ብዛት 85) በጠቅላላው 256 እና በፀሃይ ብርሃን (በሶላር) ብቻ የሚሰሩ ማቀዝቀዦዎች የተለያዩ ሞዴልና (htc40sdd) ብዛት 77 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 8ቱ ያልተተከሉ እና 5ቱ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

**28.13.** በ2011 በጀት አመት በመምሪያው በቀን 13/9/2011 የማቀዝቀዣ መሳሪያዎችን አስመልክቶ በተደረገ **የአካል ምልከታ** ብዛታቸው 5 የሚሆኑ **በኪሮሲን** (በአሞኒያ ጋዝ) እና **በኤሌክትሪክ** ብቻ የሚሰሩ የነበረና ለኦዲት እስከተደረሰበት ግንቦት 2011 አገልግሎት መስጠት አቁመው በመምሪያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከ5 አመት በላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤

**ውጤቱም** በሕክምና መሣሪያዎችና በመድኃኒት ማከማቻ ክፍሎች ላይ አላስፈላጊ የሆነ መጨናነቅን መፍጠሩ፣ ለአገልግሎት አሰጣጡ እንቅፋት መሆኑና ተገልጋዩን ለመጉላላትና ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርግ መሆኑ፤ በእናቶችና ህጻናት ጤና አገለግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ ተስተውሏል፡፡

## VIII. የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ «የቅርስ ጥበቃ፣የቱሪዝም ልማትና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አፈጻጸምን በተመለከተ»

**በክልሉ የሚገኙ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ምዝገባ፣ ቁጥጥር እና ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፣**

29. ቅርሶች ከህገወጥ የቅርስ ዝውውር ለመከላከል፣ የቅርሶችን ብዛት፣ ዓይነት፣ ስርጭትና ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ የቅርስ ምዝገባና ቁጥጥር ማከናወን እንዳለበት በ2006 ዓ.ም በአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የወጣው የቅርስ ምዝገባ ማኑዋል ገጽ 5 ይገልጻል፡፡ይህ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተውለዋል፡-

29.1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ምዝገባ ሲደረግ ቅርሱ የተሰራበት ማቴሪያል /ስሪት/ በትክክል በመሳሪያ በመለየት እንዲሁም የተቆጠረው ቅርስ በሌላ ጊዜ በሌላ ተመሳሳይ ነገር አስመስሎ ቢተካ ለመከላከል በማይቻልበት መንገድ በእይታ ብቻ በማየት የተሰራበት ውህድ ሳይረጋገጥ ስለሚመዘገብ በአግባቡ ምዝገባ እየተደረገ አለመሆኑ፡፡ /ለአብነት ጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ ላስታ ወረዳ፣ ላልይበላ ከተማ አስተዳደር፣ ሊቦ ከምከም ወረዳ/

29.2. በላስታ ወረዳ በ44 ቋሚ የቅርስ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ ብዛታቸው የማይታወቅ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች 4 ቋሚ ቅርሶች (ቀደሊ፣ አቡነ ዮሴፍ፣ ማውሬና ሳርዝና ሚካኤል) በኦዲት እስከተደረሰበት እስከ 10/03/2011 ዓ.ም ድረስ ምዝገባ ያልተደረገ እንዲሁም በወረዳው የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ምዝገባ ከ2,975 ቅርሶች ውስጥ ምዝገባ የተደረገው 1,071 (36%) ብቻ መሆኑ፤

**ውጤቱም** ቅርሶች በተመሳሳይ ቅርስ መሰል ቢተኩ መከላከል እንዳይቻል፣ በአይጥና በብል እንዲበሉ፣ የብራና መጽሐፍቶች ተገነጣጥለውና ድጉሳቸው እንዲለቅ፤ተለይተው እንዳይታወቁ፣ በግለሰቦች ቤት እንዲቀሩ እና ተሰባስበው እንዳይጎበኙና የገቢ ምንጭ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለጉዳት /ብልሽት/ከመጋለጠቸው በፊት የብልሽት መንስኤዎችን በማጥናት የቅድመ መከላከል ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤**

30. ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለጉዳት/ብልሽት/ ከመጋለጣቸው በፊት የብልሽት መንስኤዎችን በማጥናት የቅድመ መከላከል ተግባር ማከናወን ቅርሶች ለከፋ ጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት ለመከላከል እንደሚረዳ በክልሉ በ2008 የወጣ የቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንክብካቤ ማኑዋል ገጽ 33 ላይ ይገልጻል፡፡ ይህ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተስተውለዋል፡-

30.1 በደቡብ ጎንደር ፋርጣ ወረዳ የህሩይ ጊወርጊስ ቤተክርስቲያን ለተንቃሳቃሽ ቅርሶች ራሱን የቻለ እቃ ቤት ባለመሆኑ በቅርስነት የተመዘገቡ ቅርሶች ከሌሎች ንዋየ ቅድሳት ጋር ተደበላልቀው የተቀመጡ በመሆኑ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ፤ ለአብነት 10 የብራና መጽሐፍት (ታመረ ማርያም ገጾቹ የተገነጣጠሉ፣ ግብረ ህመማትና ስንክሳር የሽፋን ገበታቸው የተጎዱና ገጾቹ በአይጥ የተበሉ፣ ገድለ ጊወርጊስ በአያያዝ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው)፣ 6 ጽናዎች፣ የአፄ ዮሐንስ 4ኛ የክብር ወንበሮች ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ፤

30.2 በክልሉ ከሚገኙት ጥንታዊ የግድግዳ ሥዕሎች ውስጥ በቁጥር 9 የሚሆኑትን ለማጥናትና የስነዳ ስራ ለመስራት ታቅዶ በአንዱ ላይ ብቻ የጥናት እና ስነዳ ስራ የተሰራ እንዲሁም በ10 ዞኖች የሚገኙ ጥንታዊ ስእሎችን መረጃ ለማሰባሰብ ታቅዶ በ2 ዞኖች ብቻ የመረጃ የማሰባሰብ ስራ የተሰራ መሆኑ፤

30.3 በሊቦ ከምከም ወረዳ ዋሻ እንድሪያስ ገዳም ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ከአስር አመት በላይ አየር በማያገኙበት ሁኔታ በዋሻ ውስጥ መሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ፡

30.4 በደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኘው የደብረሲና ማርያም ቤተክርስቲያን እንዲሁም በምዕራብ በለሳ ወረዳ የሚገኘው ወይብላ ማሪያም ቤተክሪስትያን በቅርስነት የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በቂ የሆነ ማስቀመጫ የሌላችው በመሆኑ፤ደህንነታቸው አሰተማማኝ አለመሆኑና ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያመች በሚሉ ምክንያቶች በግለሰቦች ቤት እንዲቀመጡ እየተደረገ መሆኑ፤

30.5 በክልል ደረጃ፣ በጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ በላልይበላ ከተማ አስተዳደር፣ በሰሜን ወሎ ዞን እና በላስታ ወረዳ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለጉዳት ከመጋለጣቸው በፊት የጉዳት መንስኤዎችን ለማወቅ የሚያስችል ዝርዝር ጥናት እየተደረገ ከጉዳት የመከላከል ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፣

**የጎንደር ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች መምሪያ**

30.6 በፋሲል ግንብ በስተምስራቅ በኩል የሚገኙ ሶስት አገር በቀል ግዙፍ ዛፎች ያረጁ በመሆናቸው ቢወድቁ በቅርሱ ላይ አደጋ ሊያደርሱ በሚችሉበት ሁኔታ መገኘታቸው፣

30.7 በዋናው የፋሲል ቤተመንግስት ለአንድ ሰርግ ፕሮግራም ብር 3,000.00 ተከፍሎ የሚገባው የሰው ብዛት 30 ብቻ እንዲሆን በመመሪያ ደረጃ ያለ ቢሆንም በተግባር ግን እየገባ ያለው ለአንድ ሰርግ 200 ሰው እና ከዛ በላይ ስለሚስተናገድ በቅርሱ ላይ ጉዳት እየደረሰበት መሆኑ፣

30.8 ከአፄ ፋሲል ግንብ ቅርስ ጋር አብረው የተሰሩ የቅርሱ አካል የሆኑ እና በተለያዩ ጊዜያቶች ጥገና የተደረገባቸው አገር በቀል እንጨቶች በፈንገስ እና በምስጥ ከመጠቃታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራ ባለመሰራቱ በቅርሱ ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፤

30.9 በተለያዩ ጊዜያቶች በጎንደር ከተማ አስተዳደር ለሚገኙ አብያተ መንግስታትና ጥንታዊ ቤተክርስቲያናት ለምርምር የሚመጡ ተመራማሪወች የደረሱበትን ውጤት እና የማስተካከያ ሀሳቦች ለማወቅ በተቋም ደረጃ የተደረገ እንቅስቃሴ አለመኖሩ፤

**የላሊበላ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች ጽ/ቤት**

30.10 ኢንዱኮ በተባለ የጣሊያን ድርጅት ከ1999 መጀመሪያ እስከ 2000 ዓ.ም የተሰራው የላሊበላ ውቅር አባያተ ክርስቲያናት ጊዜያዊ መጠለያ ከ5-7 ዓመት ያገለግላል ተብሎ የተሰራ ቢሆንም የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት 10/03/2011 ዓ.ም ድረስ (ለ10 ዓመታት) ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ ባለመነሳቱና ነፋስ ዓመታት በሚነፍስበት ጊዜ ከፍተኛ ድምጽ የሚያሰማና የሚወዛወዝ በመሆኑ በቅርሱ ላይ የመሰንጠቅ ጉዳት እያደረሰ እና ቢወድቅ ቅርሱን ሙሉ በሙሉ ሊያወድመው የሚችል መሆኑ፤

30.11 በ2005 ዓ.ም በዘላቂ ቱሪዝም ልማት ፕሮጀክት ለትኬት ቢሮ ተብሎ የተገነባ አሁን ለላሊበላ ቤተክርስቲያናት ሙዚየም ሆኖ እያገለገለ ያለው አሰራሩ ለሙዚየሙ ተብሎ የተሰራ ባለመሆኑ ከፎቁ ላይ ሽንት ቤት ስለሆነና እርጥበት ስላለው እንዲሁም የደብሩን ቅርሶች ሁሉንም በሙዚየሙ ለማስቀመጥ ጠባብና የቅርስ ማስቀመጫው ከእንጨት መሰራት ያለበት ቢሆንም ከብረት በመሰራቱ ቅዝቃዜ ስለሚስብ ለቅርሶች ደህንነት ጥሩ ባለመሆኑ ወደ ሙዜሙ መምጣት የሚገባቸው ቅርሶች ወደ ሙዚየሙ ያልገቡ መሆኑ፤

30.12 የላሊበላ አብያተክርስቲያናት መጠለያ በ1999 መጀመሪያ ላይ ስራው በጣሊያን ኮንትራክተር ካምፓኒ ሲጀመር ውሉና ዲዛይኑ እንዴት እንደሆነ መረጃ ባይኖርም ለህዝቡ በማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድና ግንዘቤ ሲሰጥ የተገለጸው ዲዛይኑ ከቤተክርስቲያኑ ውጭ ምሰሶዎች ተተክለው ዝናብ በሚሆንበት ጊዜ የሚዘረጋ ሲፈለግ ደግሞ የሚታጠፍ እንደነበር ነገር ግን የተሰራው ክብደቱ ምን ያህል እንደሆነ ባይታወቅም በከባድ እቃ ማንሻ ማሽን ክሬን እየተነሳ የተተከለ በጣም ክብደት ያለው ብረት 4 መጠለያ ማለትም በቤተመድሃኒያለም፣ በቤተማሪያም፣ በቤተ አባ ሊባኖስና ቤተ አማኑኤል በተክርስቲያናት ዋሻ ውስጥ መጀመሪያ ከተባለው ዲዛይን ውጪ የተሰራ መሆኑ፤

30.13 በላሊበላ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ከ1999 እስከ 2000 ዓ.ም ለቤተ አባ ሊባኖስ ቤተክርስቲያን የተሰራው መጠለያ በሰሜን በኩል ያሉት ሁለቱ ምሰሶዎች ያረፉት ከአባ ልባሎስ ቤተክርስቲያን አናት እና ለቤተ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የተሰራው መጠለያ አንዱ ምሰሶ እግሩ ያረፈው ከቤተ

መርቆርዮስ ወደ ቤተ አማንኤል ወደ ሚወስደው ዋሻ አናት ላይ በመሆኑ በቤተክርስቲያኑና ዋሻው ውስጥ ምሰሶው በቆመበት በኩል አለቱ እየተላጠ እየወደቀ መሆኑ፤

**ውጤቱም** ቅርሶች ራሱን ያቻለ እቃቤት ወይም ሙዚየም ውስጥ በስርዓት ባለመቀመጣቸው፣ የቅድመ መከላከል ስራ ባለመሰራቱ ለጉዳት እንዲጋለጡ አድርጎታል፡፡

**በክልሉ ውስጥ በየዓመቱ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ቅርሶች በመለየት ለከፋ ጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት ጥገና ስለመደረጉ፤**

31. በተሟላ መረጃ ላይ በመመስረት የተበላሹ ወይም የተጎዱ ቅርሶችን በተመሳሳይ ቁስና የአሰራር ዘዴ በመጠቀም የለውጡ መጠን ሳይጎላና ታሪካዊ እሴቱ ሳይዛባ ቅርሱ ጨርሶ ሳይወድም ወደ ቀድሞ ይዘቱ መመለስ አስፈላጊ መሆኑን በክልሉ በ2008 የወጣ የቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንክብካቤ ማኑዋል ገፅ 16 ይገልጻል፡፡ ይህ ተግባራዊ መሆኑን ኦዲት ሲደረግ፤

**የአብክመ ባልና ቱሪዝም ቢሮ**

30.1 በክልሉ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ቅርሶች የጉዳት መጠናቸው እየተጠና ቅደም ተከተል ወጥቶላቸውና በቂ የጥገና በጀት ተመድቦላቸው ጥገና ስለማይደረግ በተያዘው የጊዜ ገደብ እየተጠናቀቀ አለመሆኑ፤ ለአብነት፤-

- ቢሮው ከ2009 እስከ 2011 ዓ.ም ለቅርስ ጥገና እንዲፈቀድከለት ከጠየቀው በጀት ብር 321,098,724.00 ውስጥ በክልሉ የተፈቀደለት ብር 54,400,000.00 /16.94%/ ብቻ በመሆኑ የቅርስ ጥገና በተያዘለት ጊዜ እየተጠናቀቀ አለመሆኑ::

**ሰሜን ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ**

30.2 መቄት ወረዳ የአዲስ አምባ መድሃኒያለም ቋሚ ቅርስ ላይ በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ቢደርስበትም እስካሁን ምንም አይነት ጥገና ያልተደረገለት መሆኑ፤

30.3 በጉባ ላፍቶ ወረዳ የዋሌ እየሱስ እና በዳውንት ወረዳ መዳ ማሪያም ፍልፍል የዋሻ ውስጥ ቤተክርስቲያን የፊት ለፊት መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመንሸራተት ገደላማ እየሆነ መሄድ እና ተ.ቁ 17.6 በቅርሱ አናት ላይ የሚወርደው ውሃ በጎን በኩል እያቆረ በመሆኑ እንዲሁም አለቱን በማበስበስ ውሃ ወደ ዋሻው ውስጥ በማስረግ እያንጠባጠበ ቢሆንም ምንም አይነት መፍትሄ ያልተወሰደ መሆኑ፤

30.4 በመቄት ወረዳ አይማጥ ቅድስት ስላሴ፣ ጠንበቆት መድሀኒያለም፣ አዲስ አንባ አቡነ ሙሴና ደብረሲና ቅድስት ማሪያም ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያናት ግድግዳቸውና ጣራቸው በመሰነጣጠቁ ውስጣዊ አናቱ የዝናብ ውሃ በማስገባቱ በግድግዳው ላይ ጉዳት እየደረሰ ቢሆንም ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑ፤

30.5 በዳውንት ወረዳ ቀረጥ ጊዮርጊስና ሰጎራ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን የቅኔ ማህሌት፣ የቅድስትና ቤተ መቅደስ ግድግዳና ጣሪያ መሰነጣጠቅና ፍሳሽ በማስገባቱ፤ የህንጻው የውጪ የፊት መሬት /አውደ ምህረት/ መንሸራተቱ፤የግብር ቤት ፍልፍል ህንጻ መሰንጠቅና ፍሳሽ በመግባቱ በሚሉት ምክንያቶች ቅርሱ አደጋ ላይ የወደቀና በውስጡ የሚገኙ የግድግዳ ላይ ስዕሎች የመላላጥና መደብዘዝ ችግር በመግጠሙ በቅርሱ ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፣

**የጎንደር ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች መምሪያ**

30.6 በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ጉዳት የደረሰባቸው ቅርሶች ትኩረት ተሰጥቶ ጥገና እየተደረገላቸው አለመሆኑ። ለአብነት አፄ ፋሲል ግንብ፣አፄ ፋሲል መዋኛ፣ቁስቋም ቤተክርስቲያን፣ ጠዳ እግዚአብሄር አብ ቤተክርስቲያን ለረጅም አመት በየዓመቱ እንዲጠገኑ ቢጠየቅም እስከ መጋቢት 22/2011 ዓ.ም ድረስ ጥገና አለመደረጉ፡

30.7 የፋሲል ግንብ ጥቅምት በ2011 ዓ.ም ላይ በኖራ ጥገና ሲደረግ ሙሉ ጥገናው ሳይጠናቀቅ ስራው ስለተቋረጠ የግንቡ ሰገነት ላይ የተደረገው ጥገና የወጣው ወጪ ባይታወቅም ኖራው ውሃ ባለመጠጣቱ የተሰነጣጠቀና እየተፈረፈረ የወደቀ መሆኑ፤

**የላሊበላ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች ጽ/ቤት**

30.8 የቅርስ ጥገና የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች በመልክ እንጅ በይዘት የተጠጋጋ ያለመሆን ከፍተኛ ወጭ ወጦባቸው የተጠገኑ ቅርሶች መልሰው ለጉዳት እየተዳረጉ መሆኑ፤ ለአብነት በላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከብር 19 ሚሊዮን በላይ የወጣበት በ2011 ዓ.ም ጥገናው የተጠናቀቀው የቤተ ጎለጎልታ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እና የወጣው ወጪ ባይታወቅም በ2008 የተጠገነ ቤተ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የሚጠቀሱ ናቸው።

30.9 በከተማ አስተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከ30 ዓመት በፊት ጀምሮ የተጎዱ ጥገና ሚያስፈልጋቸውን 135 ተንቀሳቃሽ ሀይማኖታዊ ቅርሶች ምንም አይነት ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑ፤

30.10 በላሊበላ ከተማ አስተዳደር ለቅርስ ጥገና የሚውል በጀት በብድር መልክ ለሌላ ተግባር እየዋለ መሆኑ፤ ለአብነት ለማንና መቸ እንደተሰጠ መረጃ ያልተገኘለት ከ2008 ዓ.ም በፊት እየዞረ የመጣ ሌጀር ላይ በተሰብሳቢ የተያዘ ብር 1,379,400.00፣ በቀን 11/09/2009 ዓ.ም ለሻማ ሽማቾች ማህበር በብድር የተሰጠ ብር 400,000.00፣ በቀን 08/10/2008 ለላስታ ላሊበላ እግር ኳስ ክለብ በብድር የተሰጠ ብር 40,000.00 በድምሩ ብር 1,819,400.00 በብድር መልክ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

30.11 በላሊበላ ቤተክርስቲያናት ውስጥ የቤተ መርቆርዮስ ቤተክርስያን ከአናቱ ላይ ሳርና ቁጥቋጡ ያበቀለና በአናቱም ውሃ የሚያስገባ ከመሆኑም በተጨማሪ በየጊዜው ቤተክርስቲያኑ አናት እየተደረመሰ መሆኑ፤

**የላስታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት**

30.12 ቀንቀኒት ሚካኤል፣ብልባላ ቂርቆስ፣ አርባእቱ እንስሳ፣ የማውሬ ጥንታዊ የዋሻ ላይ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ውስጣዊ ክፍላቸው በመሰነጣጠቅና ውሃ ወደ ውስጥ እያስገባ በመሆኑ በተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑና የትርኮዛ ኪዳነ ምህረት ፍልፍል የዋሻ ላይ ቤተክርስቲያን ምንም አይነት እንክብካቤ ተደርጎለት ስለማያውቅ የመደርመስ አደጋ ደርሶበት ወደ ፍርስራሽነት ተቀይሮ አገልግሎት መስጠት ያቆመ መሆኑ፤

30.13 የይምርሃ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ቅርስ በ2008 ዓ.ም የስዕል ጥገና ለማድረግ ከወርልድ ሞኑመንት ፈንድ 150,000.00 ዶላር ተመመድቦለት የስዕል ጥገና ጥናት የተደረገ ቢሆንም በኦዲት እስከተደረሰበት ጊዜ እስከ ህዳር ወር 2011 ዓ.ም  ድረስ ጥገና ባለመደረጉ የግድግዳና የገበታ ላይ ስዕሎች ተፋፍቀውና ደብዝዘው በመጥፋት ላይ መሆናቸው፤

**ውጤቱም** ቢሮው ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ባሉበት ሁኔታ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ተገቢውን ጥገናና እድሣት /Restoration and Preservation/ አለማከናወኑ የጉዳት መጠኑ ሳይሰፋ በቀላል ወጪና ጊዜ ጥገናውን ማከናወን እየተቻለ አለመደረጉ የጉዳት መጠናቸው እየጨመረ ከፍተኛ ወጪ፣ጊዜና ሙያዊ ክህሎት እንዲጠይቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የጥገናው ውስብስብነት ስለሚጨምር ቅርሶች ጥገናና እድሳት ሳይደረግላቸው እንዲቀሩ እና ለትውልድ ሳይተላለፉ እንዲጠፉ ያደርጋል፡፡

**ቅርሶችን በአይነትና በመጠን በመለየት ለጉዳትና ለጥፋት ተጋላጭ በማይሆኑበት ቦታ እና እንደአስፈላጊነቱ በሙዚዬም ስለመቀመጣቸው፤**

32. ቅርሶችን በተሠሩበት ቁስና ዓይነት በመለየት ለማስቀመጥ የሚያስችል ዘመናዊ መደርደሪያዎች ያሏቸው፣ የአልባሳት ቅርሶችን አንጠልጥሎ ለማስቀመጥ የሚያስችሉ፣ በውስጡ የሚገኙ ቅርሶች በቂ ብርሃንና አየር እንዲያገኙ የሚያመቹ፣ቅርሶች በአቀማመጥ ችግር ከብልና ዝገት ለመከላከል በሚያስችል መልክ ለማደራጀት የሚያስችሉ፣ የቅርስ መመዝገቢያ ባህር መዝገብ ያላቸው፣ ቅርሶችን ለመጉብኘት በሚያመች መልክ ተደራጅተው መጠነኛ ገቢ ለማስገኘት በሚያስችል አቅምና በጠንካራ ጥበቃ የተደራጁ ሙዚየሞች ወይም እቃ ቤቶች መቀመጥ እንዳለባቸው በክልሉ በ2006 ዓ.ም የወጣ የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ቁጥጥር ማኑዋል ገጽ 7 ይገልጻል፡፡ ይህ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ እነዚህ ሁኔታዎች ተስተውለዋል፡-

**የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ**

32.1. የየክልሎችን ባህል ታሪክና አኗኗር የሚያንጸባርቅ የብሔር ብሔረሰቦች መንደር ሙዚየም እንዲገነባ

በሚል ምክንያት ስለአጠቃቀሙና ቦታው የተመረጠበት ምክንያት ሳይታወቅ እና ጥናት ስለመደረጉ ማስረጃ ከክፍያው ጋር ባልተያዘበት ሁኔታ እና በክልሉ ሙዚየም ባልተገነባበት ሁኔታ ከክልል በጀት ላይ ብር 3,741,032.00 ወጭ በማድረግ በ2007 ዓ.ም በትግራይ ክልል በሀገረሰላም ወረዳ አዲገዛኢ በሚባል አካባቢ ሙዚየም እንዲገነባ ገንዘብ መተላለፉ የግልጽናትና ምክንያታዊነት ጉድለት ያለበት መሆኑ፣

32.2. በክልሉ ክልላዊ ሙዚየም ለመገንባት የዲዛይን ስራ በ2005 ዓ.ም የቅድሚያ ክፍያ ብር 150,000.00 ከአንድ የአማካሪወች ድርጅት ጋር ውል ተይዞ የተሰራ እና በ2011 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ አጼ ቴወድሮስ ክፍለ ከተማ አየር ጤና በሚባለው አካባቢ 15,600 ስኩየር ሜትር ስፋት ያለው ቦታ ተሰጥቶ የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት ቀን 13/07/211 ዓ.ም ድረስ የግንባታ ስራው ያልተጀመረ መሆኑ፣

**የጎንደር ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች መምሪያ፤**

32.3. በከተማ አስተዳደሩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በአይነትና በመጠን በመለየት እንዲሁም ምቹ በሆነ መንገድ እየተቀመጡ አይደለም። ለአብነት፤

- ቁስቋም ቤተክርስቲያን የደብር ሙዚየም ቢኖርም ክፍሉ ጠባብና መናፈሻ ስለሌለው በምቹ ሁኔታ አለመቀመጣቸው፣
- ደብረብርሃን ስላሴ ቤተክርስቲያን እቃ ቤት ውስጥ በአንድ ላይ ታጭቀው የተቀመጡ፤
- ግምጃ ቤት ማሪያም የደብሩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በግለሰቦች ቤት የተቀመጡ መሆኑ፣
- መጥምቁ ዮሃንስ የቅርስ ቆጠራ ሲደረግ ከየግለሰብ ቤት እየመጣ የሚቆጠር መሆኑ

**የላሊበላ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝም፣ ስፖርትና ወጣቶች ጽ/ቤት፤**

32.4. በላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ ቁጥራቸው በዝርዝር የማይታወቅ የብራና መጽሐፍቶች ቅጠላቸው ተገነጣጥሎ፣ ድጉሳቸው ለቆ፣ ገበታቸው ተሰባብሮ እና ጹሑፎች እየጠፉ እና በብል እየተበሉ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ።

32.5. የላሊበላ ቤተክርስቲያን በራሱ ገንዘብ በደብሩ ውስጥ ዘመናዊ ሙዚየም ለማሰራት ዲዛይን አስወጥቶ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የፌድራሉን ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ቢጠይቅም ፈቃድ ሊሰጠው ባለመቻሉ በላሊበላ ባሉ 11 አብያተክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በአቀማመጥ ምክንያት ለጉዳት እየተዳረጉ መሆኑ፡

**ጉንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም፤**

32.6. በጎንደር ከተማ የአጼ ፋሲል ቤተ መንግስት የመልካምድር ስራ/Land Scape/ና ሙዚየም የማደራጀት ተግባር ለመፈጸም ከኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ጋር በ2008 ዓ.ም ውል ተይዞ በግምት ብር 100,000.00 የሚያወጡ ጣውላዎች ተገዝተው ተግባሩ ከታህሳስ 2010 ዓ.ም ጀምሮ

ስለተቋረጠ የተገዙት ጣውላዎች ከ1 አመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡና ሙዝየሙም ያልተሰራ መሆኑ፤

**ውጤቱም** ቅርሶችን በተሠሩበት ቁስና ዓይነት በመለየት ለማስቀመጥ የሚያስችል ዘመናዊ መደርደሪያዎች፣የአልባሳት ቅርሶችን አንጠልጥሎ ለማስቀመጥ የሚያስችሉ፣ቅርሶች በቂ ብርሃንና አየር በሚያገኙበት ሁኔታ፣ ባለመቀመጣቸው በብል እንዲበሉ፤ እንዲቀዳደዱና እንዲሰባበሩ ያደርጋል፡፡

**ከየመዳረሻዎች የሚሰበሰቡ ልዩ ልዩ ገቢዎች ለአካባቢው ልማትና ለቅርስ ጥገና እየዋለ አለመሆኑ፤**

33. በጎንደር ከተማ አስተዳደር ከጎብኝዎች በ2006 ዓ.ም ብር 2,964,550.00፣በ2007 ዓ.ም ብር 5,582,851.00፣ በ2008 ዓ.ም ብር 4,304,539.00፣ በ2009 ዓ.ም ብር 3,097,070.00 እና በ2010 ብር 6,066,154.00 በድምሩ ብር 22,015,164.00 የሆነ ከፍተኛ ገቢ ቢሰበሰብም ለቅርስ ጥገና እየዋለ አለመሆኑ፡፡

33.1. የላልይበላ አብያተክርስቲያናት /11ዱ ቤተክርስያናት/ የቅርስ ባለቤቶች የቅርሱ ባለቤቶች በመሆናቸው ቅርሱን የመጠገን ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ለቅርሱ ጥገና በገንዘብ በኩል አስተዋጾ እያደረጉ አለመሆኑ፡፡

33.2. በላልይበላ ከተማ አስተዳደር ከጎብኝዎች በ2006 ዓ.ም ብር 221,917,784.12፣ በ2007 ዓ.ም ብር 181,033,500.00፣ በ2008 ዓ.ም ብር 220,789,242.00፣ በ2009 ዓ.ም ብር 147,034,797.00 እና በ2010 ብር 186,091,884.00 በድምሩ ብር 956,867,207.12 የሆነ ገቢ ቢሰበሰብም ለአካባቢ ልማትና ለቅርስ ጥገና እየዋለ አለመሆኑ፣

**ውጤቱም** በክልሉ የሚገኙ በፌድራልም ሆነ በክልል የሚስተዳደሩ ቅርሶች በገንዘብ እጥረትና ትኩረት ባለመስጠት ምክንያት ውቅታዊ ጥገና ባለመደረጉ እየተጐዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የፋሲል ግንብንና ላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያንን ብቻ በማስጎብኘት የሚገኘው ገቢ የክልሉን ቅርሶች በሙሉ ማስጠገን የሚችል ገቢ ቢሆንም ራሳቸውን እንኳን መጠገን ባለመቻሉ በመፍረስ ላይ ናቸው፡፡

**IX. በክልሉ ከተማ ል/ቤ/ኮ/ቢሮ የከተሞች ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ግንባታ ፕሮግራም አፈፃፀምና አስተዳደር፤ የጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች በጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የግንባታ ግብዓቶችን ተጠቅሞ የተገነቡ ስለማሆኑ፤**

34. በክልሉ ባሉ ከተሞች የጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ግንባታ በጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የግንባታ ግብዓቶችን ተጠቅሞ እየተገነቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ግኝቶች ታይተዋል፡፡

**በጎንደር ከተማ ከተገነቡት፤**

34.1. ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ሲገነቡ የጠጠር መሳሳትና የአላይመንት ችግር ያለባቸው መሆኑ፤ /ለአብነትም ጃን ተከል ክፍለ ከተማ/፤

34.2. መሃል አራዳ ክፍለ ከተማ ከአቶ ሜድስራው ስጦታው እስከ ሽኩር ካሳሁን የተሰራ መንገድ የመንገዱ ግድለት/ስሎፕ/ ከተፋሰሱ በተቃራኒ የተሰራ መሆኑ፤

34.3. ማራኪ ክፍለ ከተማ ጀጃው ብሎክ 3 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ የዋለለ (የረገበ፣ የሰመጠና የጎበጠ) መሆኑ፤

34.4. በአዘዞ ክፍለ ከተማ ከአብቁተ እስከ ፎከስ ት/ቤት የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ የመዋለል ችግር ያለበት /የረገበ፣ የሰመጠና የጎበጠ/ መሆኑ፤

**በደሴ ከተማ ከተገነቡት፤**

34.5. ቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ሰፈረ ሰላም ከከድጆ መስጅድ እስከ ዋና አስፓልት በ2010 በጀት አመት በብር 1,371,938.64 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ከአስፓልት ጀምሮ 85 ሜትር ርዝርመት ያክል የመንገዱ ክፍል የፈረሰ መሆኑ፤

34.6. በቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ራዲዮ ጣቢያ ከጀሚላ ሱቅ እስከ ማሞ ቤት በ2009 በጀት አመት በብር 1,599,912.35 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ምንም አገልግሎት ሳይሰጥ ሙሉ በሙሉ የፈረሰ መሆኑ፤

34.7. ቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ራዲዮ ጣቢያ ከመሰረት ቤት እስከ መምሬ ቤት አለፍ ብሎ በ2009 በጀት አመት በብር 1,595,069.32 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ የመንገዱ 70 ሜትር ርዝመት ያክል የፈረሰ መሆኑ፤

34.8. በሆጤ ክፍለ ከተማ ሃሬራ አካባቢ ከእንቁጣጣሽ ወደ ሮቢት በ2010 በጀት አመት በብር 1,534,177.35 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ መንገዱ ከጎርፍ ማፋሰሻው ጋር የተመጣጠነ ግድለት የሌለው መሆኑ

34.9. በ2010 በጀት አመት ከዚነት ቤት እስከ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን በብር 2,027,523.60 በወርቅነሽና ተስፋዬ ኮብል አንጣፊ ማህበር የተሰራ መንገድ የፈራረሰ መሆኑ፤

34.10. በቧንቧ ውኃ ክፍለ ከተማ በሰፈረ ሰላም አካባቢ የተሰሩ መንገዶች ክፍተት መስፋት/spacing/ ችግር፣ የከርብስቶን መፈራረስ፣መስጠም፣የውሃ መሄጃ ዲች ተዳፋቱን/slope/ባለመጠበቅ ውሃ ማቆር፣ ከመንገዱ መነሻ ላይ አለመታሰር፣ተዳፋት በሆኑ የኮበል ስቶን መንገዶች ላይ በቅርብ በቅርቡ አለመታሰር ችግር ያለባቸው መሆኑ፤

አሰራሩ በከተሞች የተገነቡ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ይሰጣሉ ተብሎ ከተቀመጠው የአገልግሎት ዘመን /አመት ቀድመው የሚፈራርሱ (ደሴ 1 አመት ሳያገለግሉ)፤ለመንገዶች ግንባታ የተከፈለ ገንዘብ ማስገኘት ያለበትን ያክል ጠቀሜታ ያላስገኘ፤ ለመንገዱ ተጠቃሚዎች አገልግሎት ምቹ እንዳይሆኑ ያደረገና የተደራጁ ማህበራትም በተደራጁበት የስራ መስክ ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

በከተሞች ወሰን ውስጥ የተገነቡና ጥገና የሚያስፈልጋቸው የጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ተለይተው በወቅቱ ጥገና እየተደረገላቸው ስለመሆኑ፤

35. ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉና የተጎዱ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች የመንገዶች ጉዳት ሳይባባስ አስፈላጊው ጥገና እየተደረገላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

**ጎንደር ከተማ፤**

35.1. በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 10 ለገሰ ንጉሴ አካባቢ በቀበሌ 10 ባታ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በቀበሌ 10 መብራት ሃይል ጀርባ መንገድ፤ በቀበሌ 07 ከመናኸሪያው እስከ ክፍለ ከተማው ድርስ የተሰራው ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

35.2. በጃንተከል ክፍለ ከተማ ሰላም ሆቴል አካባቢ ኮኮብ ዳቦ ቤት አካባቢ ጋሪ ተራ አካባቢ ከነጌትነት ፈንታ አካባቢ አስራት ጠብቀው አካባቢ እልልታ አካባቢ ጀለጅ ሆቴል አካባቢ ከሩፋኤል እስከ ፃድቁ ት/ቤት በአፈር የለበሰ፤ ኮብል መንገዱ የፈረሰና የተናደ፣ኮኮብ ዳቦ ቤት እስከ አስፓልት የተሰራው ጌጠኛ መንገድ አስፓልቱና ኮብል መንገዱ መገናኛው /ጆይንት/ የፈረሰ፤

35.3. በፋሲል ክፍለ ከተማ ከደብረ ሰላም እስከ ቀይ አምባ አራዳ ክፍለ ከተማ ከአቦ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ከዋርካ ሰንበቴ ቀበሌ 09 አካባቢ ከጋሪ ተራ ቀበሌ 10 ከመርቆሪዎስ ፀበል አካባቢ ከባታ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በቀበሌ 07 ከሸህ ሀሚድ እስከ ሻምበል መካው በቀበሌ 07 ከባታ ፀበል መውረጃ እስከ አሊ የሱፍ ወፍጮ ቤት መንገዱ የተሸረሸረና በአፈር የለበሰ፣በቀበሌ 09 ቀጠና 02 የተሰራ መንገድ የጎርፍ ማፋሰሻው የተጎዳ፤ አዘዞ ክፍለ ከተማ ቴሌ ሴንተር ፊት ለፊት የተሰራ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፣ ፎከስ ት/ቤት አካባቢ የተሰራ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፣ ጎመንጌ ት/ቤት የተሰራ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

35.4. መሃል አራዳ ክፍለ ከተማ ከሞኘ መቆሚያ እስከ በለሳ መውጫ ኮብል መንገዱ የፈረሰ በአፈርም የተዳፈነ፤ ከቢርጋታ መውረጃ መንገድ እስከ መርቆሪዎስ ፀበል/ቁራ መውረጃ መንገድ/ መንገዱ ከቁራ መውረጃ ጋር መገናኛ ላይ ተንዶ የፈረሰ (30 ሜትር የሚሆነው የመንገዱ የመጨረሻ አካል የፈረሰ፣ ከዋና አስፓልት /ጎቶኒያል ኮሌጅ አሰከ አውቶ ፓርክ መንገዱ በጎርፍ የተወሰደ፣ የተናደና የፈረሰ፣ ፋሲል ክፍለ ከተማ ዳራ ገዳ አካባቢ ቀበሌ 2 ከቦታነሽ እስከ ጋሻው አየልኝ ለተሰራው ጌጠኛ መንገድ የተሰራ የጎርፍ ማፋሰሻ የፈራረሰ፤

35.5. ማራኪ ክፍለ ከተማ ከቴክኒክ እስከ አስቻለው ብረታብረት ብየዳ የጌጠኛ ድንጋይ መንገዱ ከዋናው አስፓልት መገናኛ ላይ የተናደና የፈረሰ፣ ከጀጃው ሱቅ የተሰራ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ የፈረሰ፤

ቢርጋታ መውረጃ መጀመሪያ አካባቢ አስፋው ሱቅ እስከ ሃጅ እባቡ /ፍሎሬዳ/ መንገዱ በደለልና አፈር የተዳፈነ እንዲሁም ከመገናኛው ላይ የፈረሰ ሲሆኑ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ቢሆኑም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን 13/06/2011 ዓ.ም ድረስ ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑ፤

**ደሴ ከተማ አስተዳደር፤**

35.6. በሰኞ ገበያ ክፍለ ከተማ ከሃጅ ይመር ግንብ እስከ ሜጠሮ ሱቅ ድረስ፣በኮሽም በር ቀጠና 2 ሰኞ መስጊድ፣ሃያት ሰፈር አካባቢ፣በሰኞ ገበያ መዋዕለ ህፃናት አካባቢ፤በኮሽም በር ቀጠና 3 እና 4 /ድንበር/፣በኮሽም በር ቀበሌ ቀጠና 2 ሽንኩርት ተራ፣በቀጠና 8 ኮሽም በር በእነ ጋሻው ድረስ የተሰሩ፣መንገሻ መጋዝን አካባቢ፣በሶስተኛ ጣቢያ የተሰራ፣በቀጠና 7 ህንፃ ጀምሮ ት/ቤት መገንጠያ እስከ ኮሽም በር ቀበሌ፣በሳላይሽ ቀበሌ ባዝራ ግቢ የተሰራ፣ሜጠሮ ኡራኤል ቤ/ክርስቲያን በላይና በታች የተሰሩ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች በ2010 በጀት አመት  ጀምሮ እንዲጠገኑ ቢጠየቅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ያልተጠገኑ መሆኑ፤

35.7. በሆጤ ክፍለ ከተማ ከመብራ ኃይል እስከ ኮንዶሚኒየም የተሰራው ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ መነን ት/ቤት ፊት ለፊት የመንገዱ 30 ሜትር ያክል በገረጋንቲ የተዳፈነና 10 ሜትር ርዝመት የሚያክል ጌጠኛ ድንጋዩ የፈረሰ መሆኑ፤

ሁኔታው የተጎዱ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶችን በየበጀት አመቱ በወቅቱ እንዲጠገኑ አለመደረጉ የመንገዶችን ጉዳት የበለጠ እንዲባባስ የሚያደርግ መሆኑ፤ የጉዳቱ መጠን በጨመረ ቁጥር መንግስትን ለከፍተኛ የጥገና ወጭ የሚዳርግ መሆኑ፤ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የአገልግሎት ምቾት የማይሰጥና መንገዱ ማገልገል ያለበትን ያክል ሳያገለግል ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ያደርጋል፡፡

**የጌጤኛ ድንጋይ /cobble stone/ መንገዶች በቂ የጎርፍ ማፋሰሻ ፣የድጋፍ ግንብ እና ሌሎች እስትራክቸሮች ተሟልተው የተገነቡ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

36. በከተሞች የተገነቡ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች የጎርፍ ማፋሰሻ፣የድጋፍ ግንብ እና አስፈላጊ የሆኑ እስትራክቸሮች ተሟልተው የተገነቡ ስለመሆናቸው ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተውለዋል፡፡

**ጎንደር ከተማ፤**

36.1. በጃንተከል ክፍለ ከተማ በ04 ቀበሌ ከጫልቱ ቤት አስከ ማሬ ተከስተ ተብሎ የሚጠራው የኮብል እስቶን መንገድ፤ ከፃድቁ ዮሃንስ ፊት ለፊት የተሰራው የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

36.2. ፋሲል ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ቀጠና 02 ዳራገዳ አካባቢ የተሰራ የጌጠኛ ድንጋይ፤ከስላሴ አስፓልት እስከ አርባቱ እንስሳ ለተሰራው ጌጠኛ ድንጋይ፤ ቀበሌ 02 ቀጠና 02 ዳራገዳ አካባቢ የተሰራ የጌጠኛ

ድንጋይ መንገድ፤

36.3. መሃል አራዳ ክፍለ ከተማ ከአቶ ሜድስራው ስጦታው እስከ ሽኩር ካሳሁን የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤በቀበሌ 10 ቢርጋታ መውረጃ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋ መንገድ፤ ማራኪ ክፍለ ከተማ ከመስጊድ እስከ ኮሌጅ ማዞሪያ የተሰራ የመንገድ፤ ከዘይት ፋብሪካ እስከ ልደታ ድልድይ የተሰራ መንገድ፤በአዲስ አለም ቀበሌ 08 የተሰራው ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤በቀበሌ 10 መርቆሪዎስ እና ግንቦት 20 ጤና ጣቢያ አካባቢ የተሰሩ የጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች፤ቢርጋታ መውረጃ መጀመሪያ አካባቢ አስፋው ሱቅ እስከ ሃጅ እባቡ/ፍሎሬዳ/ የተሰራ መንገድ፤

36.4. በአርበኞች ክፍለ ከተማ ፎገራ አካባቢ (ኪቢአድ አካባቢ) የተሰሩ መንገዶች፤ቀበሌ 2 ዳራ ገዳ አካባቢ ከቦታነሽ እስከ ጋሻው አየልኝ የተሰራ መንገድ እና በዞብል ክፍለ ከተማ የድሮው ቀበሌ 14 ወንፊት ተራ የተሰሩ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች፤

ከላይ የተዘረዘሩ መንገዶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት 13/06/2011 ዓ.ም ድረስ ያለጎርፍ ማፋሰሻ የተሰራ መሆኑ፤የጎርፍ ማፋሰሻ ያልተሰራላቸው፣የጎርፍ ማፋሰሻ የተሰራላቸው ማፋሰሻ የአካባቢውን ጎርፍ መሸከም የማይችልና የጎርፍ ማፋሰሻው ግድለቱን የጠበቀ አለመሆን እንዲሁም የተፋሰስ ከፍታው ከመንገዱ ከ10-15 ሳ.ሜ ከፍ ብሎ መሰራት ሲገባው ከመንገዱ በታች እስከ 4 ሳ.ሜ ድረስ ዝቅ ብሎ የተሰራ መሆኑ፤

36.5. ጃንተከል ክፍለ ከተማ ከጫልቱ ቤት እስከ ማሬ ተከስተ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤ከማሬ ተከስተ እስከ አርባዕቱ እንስሳ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ እና ፋሲል ክፍለ ከተማ ከአስፓልት በላይኛው ድልድይ እስከ ገብርኤል የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የድጋፍ ግንብ ያልተሰራላቸው መሆናቸው፤

36.6. መሃል አራዳ የቢርጋታ መውረጃ መንገድ ለተሰራው ተፋስስ መጨረሻና የባታ መውረጃ መንገድ መገናኛ ላይ፤በጃንተከል ክፍለ ከተማ ከጣና ግሮሰሪ እስከ ሙሓመድ ቤት የተሰራ መንገድ ላይ እና አዘዞ ክፍለ ከተማ ከመብራ ሃይል እስከ አዘዞ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2009 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት 13/6/2011 ዓ.ም ድረስ እስላብ ከልቨርት ያልተሰራላቸው መሆናቸው፤

36.7. ፋሲል ክፍለ ከተማ ከደብረ ሰላም እስከ ቀይ አምባ ት/ቤት ለተሰራው መንገድ የውሃ ማፋሰሻ በዩ ልባስ እንዲሰራለት የአካባቢውን ነዋሪ ቢጠይቅም ያልተሰራለት መሆኑ፤

**ደሴ ከተማ፤**

36.8. በአራዳ ክፍለ ከተማ በሳጥን ተራ በ2008 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤ከሙሃባ ሱቅ እስከ ኑሬ ሊያቢያጆ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤ከዮናስ ጋራጅ እስከ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

36.9. ቢንቢ ውሃ ክፍለ ከተማ ከዳንዲ ቦሩ ድልድይ አድማ ብተና ቁጥር 1 በ2009 በጀት አመት በብር 1,726,235.10 የተሰራ መንገድ፤ሰፈረ ሰላም ከከድጆ መስጅድ እስከ ዋና አስፓልት በ2010 በጀት አመት በብር 1,371,938.64 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤ራዲዮ ጣቢያ ከመሰረት ቤት እስከ መምሬ ቤት አለፍ ብሎ በ2009 በጀት አመት በብር 1,595,069.32 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

36.10. በሆጤ ክፍለ ከተማ ሃሬራ አካባቢ ወደ ወፍጮ ቤቱ የተሰሩ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች፤ በሆጤ ክፍለ ከተማ ከአራዳ ድንበር ወደ ቂራ መውሰጃ የተሰራ መንገድ፤ዘማጌል አካባቢ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤

36.11. በሰኞ ገብያ ክፍለ ከተማ የድሮው ገብያ አካባቢ የተሰራ መንገድ፤በ2006 በጀት አመት ቀበሌ 08 ማዕከል ከዜብራ ድልድይ በክድጃ ሀሰን ቤት እስከ ቀበሌ 07 ማዕከል ድንበር በተሃድሶ ኮብልስቶን ንጣፍና ማህበር በብር 1,213,299.88 ለተገነባ ጌጠኛ ድንጋ መንገድ፤ዘማጌል አካባቢ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች፤ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት 04/10/2011 ዓ.ም ድረስ የጎርፍ ማፋሰሻ ያልተሰራላቸውና የአካባቢውን ጎርፍ መሸከም የማይችል መሆኑ፤

36.12. በአራዳ ክፍለ ከተማ በአባዚመሬ አካባቢ በ2008 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤በሰኞ ገብያ ክፍለ ከተማ መዋዕለ ህፃናት አካባቢ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ፤በቢንቢ ውሃ ክፍለ ከተማ ከካራ ጉቱ ኮንዶሚኒየም እስከ መሰረተ ክርስቶስ በ2010 በጀት አመት በብር 2,042,877.23 የተሰራ መንገድ፤ ከጀማል ሱቅ አለፍ ብሎ መንገሻ ጎራ በ2008 በጀት አመት በብር 1,493,684.40 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ (በታች በኩል ድጋፍ ግንብ ባለመሰራቱ የመንገዱ 20 ሜትር ያክል የተናደ)፤

36.13. በቢንቢ ውሃ ክፍለ ከተማ ከኬላ ዋና አስፓልት እስከ ራዲዮ ጣቢያ ቁጥር 1 በ2009 በጀት አመት በብር 1,452,686.55 የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ 20 ሜትር ርዝመትና 2 ሜትር ወርድ የመንገዱ ክፍል የተደረመሰ/የተናደ/ እና ከህፃናት አድን ድርጅት እስከ ብረት ድልድይ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ ድጋፍ ግንብ መሰራት እያለበት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት 04/10/2011 ድረስ ያልተሰራላቸው መሆኑ፤

36.14. በአራዳ ክፍለ ከተማ በወጣቶች መዝናኛ በሳጥን ተራ አካባቢ የተሰራ ጌጠኛ ድንጋ መንገድ ስላብ ከልቨርት መሰራ እያለበት ያልተሰራለትና በእንጨት ርብራብ እያገለገለ መሆኑ፤

ይህም አሰራሩ ከሚገነቡ ጌጠኛ ድንጋይ መንገዶች ጋር መሟላት ያለባቸውን ስትራክቸሮች ተሟልተው እንዳይሰራ ያደረገ መሆኑ፤ የግለሰቦችን ቤት እንዲንጠለጠል ያደረገና በናዳና መንሸራተት ለጉዳት የሚዳርግ መሆኑ፤የመንገድ ተጠቃሚ ማህበረሰቡ በክረምት ወቅት በጎርፍ መጥለቅለቅ ያጋለጠ መሆኑ፤መንገዶች ማገልገል ያለባቸውን ያክል ጊዜ ሳያገለግሉ በጎርፍ፣ በአፈር ናዳና መሸርሸር እንዲጎዱ ያደረገ መሆኑ፤ለተሽከርካሪና ለማህበረሰቡ እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁኔታን የፈጠረ መሆኑ፤

በአጠቃላይ መንግስት ለመንገዶች ያወጣው ወጭ መስጠት ያለበትን ያክል ጠቀሜታ ሳያስገኝ እንዲቀር ያደረገና መንገዶች በአግባቡ እንዳያገለግሉ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

## X. የአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር ስራዎች ዉጤታማነትን በተመለከተ፤

### ለኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ለሚዉሉና ወደ ዉጭ ሀገር ገብያ በሚላኩ ምርቶች ላይ ጥራታቸዉን ለማሻሻል አስፈላጊዉ ምርምር መካሄዱን በተመለከተ

37. የግብርናዉን ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪዉ ለማሸጋገር ለኢንዱስትሪዉ በጥሬ ዕቃነት ሊዉሉ የሚችሉ ምርቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሰራት እንዳለበት ይታመናል፡፡ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

#### ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል

37.1. ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ለምርምር ስራ የሚዉል ዘር እና በምርምር ተባዝቶ ወደ አርሶ አደሩ የሚሰራጭ ዘር በጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ሳያልፍና የጥራት ቁጥጥር ሳይደረግበት ወይም የዘር ደረጃ መስፈርቶችን ሳያሟላ ለአገር ዉስጥ ገበያ የሚቀርብና የጥራት ደረጃዉን ያልጠበቁ ዘሮች አርሶ አደሮች የሚጠቀሙ መሆኑ፤

37.2. የጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል በ2007 ዓ/ም የብቅል ገብስ ሙከራ ከስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል የተላከላቸዉ ቢሆንም የዘር ጥራት የሌለዉ መሆኑ፤

37.3. በጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል በ2009 ምርት ዘመን በተካሄደ የመስክ ስራ በመተማ ንዑስ ማዕከል የሚካሄዱ የሰሊጥ ሙከራዎች የብቅለት ችግር ያለ መሆኑ፤

#### አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል

37.4. በአዴት ግብርና ምርምር ማዕከል በተሰጠ የዝርዝር ኦዲት መጠይቅ ለኢንደስትሪ ግብዓትነት ለሚዉሉና የዉጭ ምንዛሬ ለሚያስገኙ ሰብሎች (አኩሪ አተር፣ የዳቦ ስንዴ፣ የመኮረኒ ስንዴ፣ ሰሊጥ) ላይ በሚፈለገዉ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶ የማይሰራ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

**ይህም** የጥራት ደረጃዉን ያልጠበቀ ምርት በመመረቱ አርሶ አደሩ ካመረተው ምርት ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጓዋል፡፡የምርት መቀነስ፤ገበያ ላይ ተወዳዳሪ አለመሆን፤ ለፋብሪካዎች በቂ ጥሬ እቃ እንዳይኖርና ከውጭ እንዲያስገቡ ሆኗል፡፡ምሳሌ የቢራ ገብስና የማኮረኒ ስንዴ፤የዳቦ ስንዴ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡

**በሰብሎች ላይ ጉዳት እያስከተሉ ያሉ የሰብል በሽታዎች(ፀረ ሰብል ተባዮች) ላይ ሳይንሳዊ ጥናት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፡-**

38. የሰብል ቴክኖሎጅ ምርምር ሙከራዎችን ለማከናዎን የሚያስችል ቤተ ሙከራ (ላብራቶሪ)መኖሩን በተመለከተ፡-

**ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል**

38.1. የጎንደር ግብርና ምርምር ችግር ፈች የሆነ ምርምር ለማካሄድ የተሟላ ላብራቶሪ ባለመኖሩ የምርምር ውጤቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፡፡ለአብነትም የበሽታ ልየታና መከላከል ሙከራዎችን፣የብሪዲንግ ሙከራዎችን ለመስራት የተሟላ ቤተ ሙከራ የሌለ መሆኑ፡፡

38.2. ለጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል በተሰጠ የዝርዝር የኦዲት መጠይቅ ላይ እንደተገለፀዉ የምርምር ስራዎችን ዉጤታማ ለማድረግ ለምርምር ስራዉ አስፈላጊ የሆነና ደረጃዉን የጠበቀ ቤተ ሙከራ ሊኖር የሚገባ ቢሆንም በጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል የተሟላ ቤተ ሙከራ ባለመኖሩ ሙከራዎችን ለማሰራት ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ መሆኑ፤

**ስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል**

38.3. የስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል ለሚሰራቸዉ የተለያዩ የሰብል ምርምር ሙከራዎች የንጥረ ነገር ይዘታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተሟላ የመፈተሻ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ችግሩን ለመፍታት ለተለያዩ የምርምር ማዕከላት የላብራቶሪ ፍተሻ እንዲደረግለት በተለያዩ ደብዳቤዎች የጠየቀ መሆኑ፡፡

**አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል**

38.4. የተለያዩ የሰብል ምርምር ሙከራዎች የንጥረ ነገር ይዘታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመፈተሻ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ችግሩን ለመፍታት ለተለያዩ የምርምር ማዕከላት የላብራቶሪ ፍተሻ እንዲደረግለት በተለያዩ ደብዳቤዎች የጠየቀ መሆኑ፡፡ለአብነትም በ2011 በጀት ዓመት የሱፍ ሙከራ የዘይት ይዘት መጠን እንዲሰራለት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከልን የጠየቀ መሆኑና ችግሩ አሁንም ያለ መሆኑ፡፡

**ውጤቱም** የቤተ ሙከራ ዕቃዎች ባለመሟላታቸዉ የምርምር ማዕከላት ለሚሰሯቸዉ የተለያዩ የሰብል ምርምር ሙከራዎች የንጥረ ነገር ይዘታቸዉን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣ የበሽታ ልየታና መከላከል ሙከራዎችን፣ የብሪዲንግ ሙከራዎችን መስራት ያልተቻለ መሆኑ፤ የተሟላ የመፈተሻ ላብራቶሪና መሳሪያዎች ባለመኖራቸዉ ችግሩን ለመፍታት ለተለያዩ የምርምር ማዕከላት የላብራቶሪ ፍተሻ እንዲደረግላቸዉ በተጨማሪ ወጭ ሌሎች አካላትን በመጠየቅ ላይ ይገኛል፡፡

## የማጠቃለያ አስተያየት፡-

- የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና ተገቢ የሆነ የአፈፃፀም መርሃ ግብር በማዘጋጀት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰዱ፣ በቀጣይም ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች እንደ መነሻ በመወሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው በየሪፖርቶቻችን በዝርዝር አሳስበናል፡፡
- ስለሆነም በኦዲቱ የተመለከቱትን ግኝቶችና የአሰራር ክፍተቶች በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ኦዲቱ እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሚመለከታቸው አካላትና በም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ክትትል እንዲደረግባቸው እያሳሰብኩ የተከበሩ አፈ-ጉባዔ፣ የም/ቤት አባላት፣ የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በስራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም
- የመ/ቤታችን የስራ ሃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና መላው ሰራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተመላከቱ የስራ ውጤቶች ላደረጋችሁት ጥረት በራሴና በአማራ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ስም ምስጋናየን በማቅረብ ሪፖርቱን በዚህ አጠናቅቃለሁ፡፡

**"አመሰግናለሁ"**

**ስመኝ ካሴ እንደሻው (አቶ)**
**ም/ዋና ኦዲተር**